# ሁለንተናዊ አካታች ስርዓት ለሁሉ

# (Integration för alla)

ከአካል ጉዳተኛ ስደተኞች ጋር ለሚገናኙ ሁሉ ታስቦ የቀረበ መጽሐፍ

በቀላል ቋንቋ
የተዘጋጀ

ISBN 978-91-639-7284-3

Layout & Grafik: Sooz Romero

Illustrationer: Maria Fröhlich

በቀላል ቋንቋ በ  Moa Candil የተጻፈ

ህትመት : Exellent Print & Design, 2020-05-07

---

አማርኛ ትርጉም በተስፋዬ ድሪባ

ጽሁፍ በብሩክ ውብሸት

ግራፊክ እና ሌይአውት ዳዊት ድሪባ

# ማውጫ


መግቢያ ........ 3

**1. እራስን መቻልና ስልጣን ........ 5**

የራስ ችሎ መኖር እንቅስቃሴ ........ 7

እራስን ችሎ መኖር እንደ መርህ ........ 7

አካል ጉዳተኛ ስደተኞች በደህና ይምጡ ........ 7

የጁሊዩስ ነቶቡሀ ልምምዶች በስዊድን ........ 9

ስልጣን ........ 10

ቅይጣዊ ትንታኔዎች ........ 11

ሁለንተናዊ ተሳትፎ - አሳታፊ ስርአት ለሁሉ ........ 12

**2. ስደትና መብቶች በስዊድን........ 14**

አስፈላጊ ቃላት ከነፍቻቸው ........ 15

ስደተኛ ........ 15

መቋቋም ........ 15

አካል ጉዳት ........ 16

አካላዊ ዝንፈት ........ 16

ከተለመደው ያፈነገጠ አካል ብቃት........ 16

ተደራሽነት ........ 17

ሰብአዊ መብቶች ........ 17

አስፈላጊ ህጎች በስዊድን ........ 17

ምቹ ዋስትና ........ 18

ፍርድ ቤቶች ........ 18

የተባበሩት መንግስታት ........ 19

የአውሮፓ ስምምነት........ 19

ልዩ ልዩ የመኖሪያ ፈቃዶች ........ 19

ስደተኞች ........ 20

ከለላ ፈላጊዎች ........ 20

ስደተኛ ........ 20

አማራጭ ከለላ ፈላጊዎች ........ 21

ልዩ ትኩረት ፈላጊዎች ........................................................................................................ 21
አዲስ መጥ .................................................................................................................. 21
ወረቀት አልባ ................................................................................................................ 21
ስራ ወይም ትምህርት .................................................................................................... 22
ቤተሰብ በስዊድን ......................................................................................................... 22
ተመልሶ መሄድ ............................................................................................................. 22
መስተንግዶና መቋቋም ..................................................................................................... 23
አካል ጉዳት ያላቸው ስደተኞች ......................................................................................... 23

የራስን እድል መወሰን ....................................................................................................... 24
ማህበራዊ አገልግሎት ህግ ................................................................................................... 24
LSS በመባል የሚታወቀው ህግ ............................................................................................ 24
የጉዞ አገልግሎት ............................................................................................................ 25
የትምህርት መብት ......................................................................................................... 25
የመኖሪያ መብትን በሚመለከት ........................................................................................... 26
ስለ ትርፍ ጊዜና ባህላዊ መብት ............................................................................................ 26
ስለ ጤና መብት .............................................................................................................. 27
የጤናና የበሽታ እንቅስቃሶ ህግ ............................................................................................ 27
ሊሎች ጤና ጥበቃ ነክ ህጎች ................................................................................................ 27
LMA ህግ .................................................................................................................... 28

ማን ምን ይሰራል .......................................................................................................... 28
የስደተኞች ባለስልጣን ......................................................................................................... 28
የስራ ስምሪት ባለስልጣን ..................................................................................................... 29
የመድህን ባለስልጣን ......................................................................................................... 29
የወረዳና የክፍለ ሀገር መስተዳድሮች ........................................................................................ 29
ህግ አዋቂዎች ............................................................................................................... 31

**3. ችግሮችና ሊሻሻሉ የሚገባቸው ........................................................................................... 33**
ብዙዎች ጤንነት አይሰማቸውም ........................................................................................... 34
ታሪኮች ........................................................................................................................... 34
የጋራ አካታች ስርዓት እንቅፋቶች ........................................................................................... 36
ባስፈላጊነት ሊታሰብባቸው የሚገቡ ........................................................................................... 39
ነገር እንዳሰቡት ሲሆን ........................................................................................................ 39

የጥምረት ስራ ሃሳቦች ........................................................................................................ 40
የኛ ሃሳቦች ........................................................................................................................ 40
አስፈላጊ መጽሃፍ ................................................................................................................ 42

**4. መደምደሚያ ...................................................................................................... 43**
ማጣቀሻ ............................................................................................................................ 45
የግርጌ ማስታወሻ .................................................................................................................. 46

መጽሐፉ ፣ አካል ጉዳተኛ ስደተኞች በደህና ይምጡ በሚባለው በ DRW ፕሮጀክት ስር የተዘጋጀ ነው። DRW ደግሞ "እራስን ችሎ መኖር " (Stiftelsen Independent Living Institute) በተባለው ድርጅት ከ Allmänna Arvsfonden በተገኘ ገንዘብ የሚመራ ኢንስቲቱት ነው።

ጽሑፉ በ **Sooz Romero ፣ Ola Linder ፣ Riitta-Leena Karlsson እና Jamie Bolling**
ተዘጋጅቶ ቀርቧል።
**Linda Robertsson** ጠቃሚ ሀሳቦችን በማበርከትና በእርማት አግዛለች።
**Julius Ntobuah Mvenyi እና Rahel Abebaw Atnafu** ለዚህ መምሪያ መጽሐፍ ጠቃሚ ይዘት ያላቸው አስተዋጽዖችን አበርክተዋል።

አሁን የሚያነቡት፣ አጠር ብሎ በቀላል ስዊድንኛ የተጻፈውን መጽሐፍ ነው።
የመጽሐፉ ዋና ርእስ ፣ " **ወደ ሁለንተናዊ አካታች ስርዓት የሚመሩ መንገዶች** " **(Vägar mot ömsesidig integration)።**
ሙሉውን መጽሐፍ በዚህ ድረ ገጽ ያገኙታል። https://wp.me/a9IOMJ-C3

በቀላል ስዊድንኛ ለሁሉ የቀረበው ይህ መጽሐፍ ከድረ ገጹ ሊወርድ ይችላል።
መጽሐፉን ከደራሲዎቹ ፈቃድ ውጪ መሸጥ በጥብቅ የተከለከለ ነው። ያለ መጽሐፉ ባለቤት (ኮፒራይት) የመጽሐፉን ይዘት መቀየር አይፈቀድም።
ስለ መጽሐፉ ጥያቄ ቢኖርዎት በሚከተለው አድራሻ ይጻፉ ወይም ይደውሉ።

Independent Living Institute: +46736794273
Storforsplan 36, 123 47 Farsta
e-post: info@disabledrefugeeswelcome.se
Independent Living Institutes hemsida: independentliving.org
Disabled Refugees Welcomes hemsida: disabledrefugeeswelcome.se

DISABLED REFUGEES WELCOME



ለዚህ መጽሐፍና ፕሮጀክት አስተዋጽዎ ላደረጉ
ድንቅ ሰዎች ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋና ይድረስ።

*Stockholm, April 2020*

## መግቢያ

ሰብአዊ መብቶች በራሳቸው አይመጡም። እኛ በ DRW (አካል ጉዳተኛ ስደተኞች በደህና ይምጡ) ፕሮጀክት የምንሰራ፣ ሰብአዊ መብታቸው እንደሚገባ ካልተከበረላቸው ብዙ ሰዎች ጋር እንገናኛለን።

ባለስልጣኖችና የወረዳ መስተዳደሮች ስራቸውን አልሰሩም። አስፈላጊው ድጋፍ ስለተደረገላቸው ሰዎች አስደሳች ታሪኮችን ሰምተናል።

አካል ጉዳተኛ ስደተኞች ብዙ ጊዜ በሰቅጣጭ ነገሮችና አድሎ በተመላበት ልምምድ ውስጥ አልፈዋል። በስዊድን ውስጥ የተሻለ ምቾት ያገኙ ዘንድ ይገባል። ሰብአዊ መብታቸው ተጠብቆ በክብርና በእውቅና መስተናገድ አለባቸው።

ያኔ ታዲያ እንደሌሎቹ በስዊድን ውስጥ ያሉ፣ እኩል መብትና ግዴታ ያላቸው ሰዎች አካል መሆን ይችላሉ።

ይህ መጽሐፍ፣ ከአካል ጉዳተኛ ስደተኞች ጋር ለሚገናኙ ባለስልጣኖችና ድርጅቶች ድጋፍ እንዲሰጥ ታስቦ የተጻፈ መጽሐፍ ነው።

መጽሐፉ ሦስት ክፍሎች አሉት። በመጀመሪያው ክፍል በስልጣንና በተለያዩ ቅቡል ያስተሳሰብ ልማዶች ዙሪያ የተለያዩ ሀሳቦች ፣

በሁለተኛው ክፍል ማህበረሰቡ ወደ ስዊድን ለሚመጡ አካል ጉዳተኛ ስደተኞች ሊሰጣቸው በሚገባ መረጃዎች ዙሪያ፣

በሦስተኛውና በመጨረሻው ክፍል አንባቢው በድርጊት የሚታየው ሁኔታ ምን ይመስላል በሚለው ሃሳብ ዙሪያ ከተለያዩ ገጠመኞች ጋር ይገናኛል።

ባለስልጣኖች በስራቸው ምን ያህል ስኬታማ ናቸው? ምን ምንስ ሊሻሻል ይችላል?


Södertörns högskola
udentre - Alfred Nobels alle 7 - Moas Båge

# 1. እራስን መቻልና ስልጣን

እራስን ችሎ መኖር አንድ አይነት እንቅስቃሴ ርእዮተ አለምና ህጋዊ መብት ነው። በመቀጠል በዚህ ዙሪያ ተጨማሪ ሀሳቦችን ማንበብ ይቻላል። እንደዚሁም ስለ DRW ፕሮጀክት  እናወራለን። አስፈላጊ ቃላትና አገላለጾችን እናብራራለን።

## የራስ ችሎ መኖር እንቅስቃሴ

ይህ እንቅስቃሴ በ 1950ቹ በአሜሪካ ተጀመረ። ብዙዎቹ በፖሊዮ በሽታ ተይዘው ነበር። በዚህ ምክንያት አብዛኞቹ ሰዎች በኢንስቲትሽኖች  ውስጥ ለመኖር ተገደዱ ። እንቅስቃሴው ይህን ይቃወም ነበር። ይህ እንቅስቃሴ ወደ ሌሎችም  የአለም ክፍሎች ተዛመተ። ይህም ለአካል ጉዳተኞች በጣም አስፈላጊ ሚና ተጫውቷል። ጉዳዩ የራስን ሕይወት በራስ የመወሰን መብትን ይመለከታል። እንደዚሁም ልክ እንደማንኛውም ሰው የህብረተሰቡ አካል የመሆን መብትንም ይጨምራል። ባሁኑ ጊዜ ይህ ራስን ችሎ መኖር እንቅስቃሴ ከእንቅስቃሴም ያለፈ ነው። ሰብአዊ መብትም ጭምር ነው። ይህም በአካል ጉዳተኞች ውል (Funktionsrättskonventionen)[1] አንቀጽ 19 ላይ ተደንግጓል።

## እራስን ችሎ መኖር እንደ መርህ

የራስን እድል መወሰንና የገዛ ምርጫን መከወን ራስን ችሎ የመኖር አስፈላጊ ክፍል ነው። ለምሳሌ ግለሰቡ ራሱ የሚፈልገውን እርዳታ ማግኘት ሊሆን ይችላል።

በተጨማሪም ማህበረሰቡ ለሁሉ ሰው ተስማሚ በሆነ መንገድ መገንባት አለበት። እኩልነት የሰፈነበትና አድሎ የሌለበት መሆን ይገባዋል። አላማው አካል ጉዳተኛ ሰዎች ተመሳሳይ እድሎች፣መብቶችና ልክ እንደሌሎቹ በአንድ አይነት መንገድ ህይወታቸውን መቆጣጠር እንዲችሉ ነው።

## አካል ጉዳተኛ ስደተኞች በደህና ይምጡ

DRW የሚለው ምህፃረ ቃል በእንግሊዝኛ Disabled Refugees Welcome ሲሆን ትርጓሜውም አካል ጉዳተኛ ስደተኞች በደህና ይምጡ የሚለውን ሀሳብ  ይገልጻል። ሁሉ ነገር የተጀመረው ጁሊየስ ንቱቡዋህ ከአዶልፍ ራትዝካ ጋር በተገናኙ ጊዜ ነበር። ጁሊየስ ስደተኛ ሆኖ ወደ ስዊድን መጣ። ሰውነቱ እንደሚገባ እንዳይታዘዝለት የሚያደርግ የአካል ጉዳት አለበት። አዶልፍ ራስን ችሎ መኖር (Independent Living Institute) ተብሎ የሚጠራው ድርጅት መስራች ነው። ጁሊየስ ለእሱ ወደ ስዊድን መምጣት እንዴት ይመስል እንደነበር ይናገራል። በነዚህ በሁለት ሰዎች የጋራ ትብብር የ DRW ፕሮጀክት ሊቋቋም ቻለ።

---

[1] https://www.ohchr.org/en/hrbodies/crpd/pages/crpdindex.aspx

ለአካል ጉዳተኛ ስደተኞች ጥቅም ተብሎ ነው።

ይህ ግሩፕ በስደተኞች ፖለቲካ መርህ ምንም ትኩረት ያላገኘ ግሩፕ ነው። DRW ይህንን መለወጥ ይፈልጋል።ፕሮጄክቱ አካል ጉዳተኛ ስደተኞችን ለመቀበል የሚያስችሉ አዳዲስ መላዎችን ይፈልጋል። ዓላማው ለነሱ የሚያስፈልገውን ድጋፍ በመስጠት የህብረተሰቡ አካል ማድረግ ነው።

**DRW በአቅም ግንባታ[2] ዙሪያ ይሰራል።** ይህም ማለት ለሰዎች ድጋፍ በመስጠት በራሳቸው ሕይወት ላይ ያንበሳነቱን ድርሻ እንዲቀዳጁ ማድረግን ይመለከታል። ለምሳሌ በራሳቸው ሁኔታ ካሉ ሌሎች የነሱን ቢጤ በመፈለግ ተገናኝቶ መተዋወቅ፣ መፍትሄዎች መፈለግ፣ አብሮ በመታገል ለውጥ እንዲመጣ መጠየቅ። አካል ጉዳተኛ ስደተኞች መድልኦ እንደሚደርስባቸው የታወቀ ነገር ነው። DRW ይህንን ነገር ለማስቆም ይፈልጋል። DRW የነገሩ ሰለባ ከሆኑ ሰዎች ጋር ይሰራል። በተጨማሪም ከመንግስት ባለስልጣኖች ጋር፣ ከወረዳዎች መስተዳድር፣ ከግል ድርጅቶች ጋር በጥምረት ይሰራል።

**የስራው ጽንሰ ሀሳብ የተመሰረተው በሰብዓዊ መብቶች** ላይ ሲሆን፣ እነዚህንም ማፍረስ ለማንም አይፈቀድም። ቢሆንም ግን የሚያሳዝነው ህጉ አለመከበሩ ነው ።

ስራው ጤናን ይመለከታል።
ጤና ስልጣንን ይመለከታል። አንድ ሰው ያለው የገንዘብ መጠንና የት ቦታ መወለዱ በጤናው ላይ የሚሳድረው ተጽእኖ አለው። እንደዚሁም የሰውየው የግል ጤንነት[3] በትምህርት ቤቱ ውጤቱ ላይና በስራ ገበታው ላይ ይገለጣል።

DRW ለሁሉ ሰው ክፍት ነው!
ቤተሰቦች፣ ወዳጆች፣ እንደዚሁም በአካታች ተሳትፎና በአካል ጉዳት (funkis) ጉዳይ ዙሪያ ለሚሰሩ ሁሉ ነው ።

---

[2] Health Literacy - teori och praktik i hälsofrämjande arbete: av Karin C. Ringsberg, s.28.

[3] Health Literacy - teori och praktik i hälsofrämjande arbete: av Karin C. Ringsberg.

## የጁሊዩስ ነቶቡህ ልምምዶች በስዊድን

ወደ ስዊድን አገር ለመምጣት ሁሌ አልም ነበር። እኔ ስዊድንን የማያት  የነበረው ሰብአዊ መብቶች የሚከበሩባት አገር እንደሆነች ነበር። ነገር ግን ከመጣሁ በኋላ የገጠመኝ የእውቀት ማነስ፣ ጭፍንነትና ከባድ ጫናዎች ማሳደር ነበር። ከልጅነቴ ጀምሮ ከፖሊዮ ጉዳት ጋር አብሬ ኖሬአለሁ።

አንደኛው እግሬ እንደሚገባ አይታዘዝልኝም። የስደተኞች ቢሮ ከተመዘገብኩ በኋላ ወደ ምኖርበት ቤቴ እንድሄድ ተፈቀደለኝ። እኔም በዚህ ነገር እጅግ ተደሰትኩ። ወቅቱ ብርድና በጣም ቀዝቃዛ ቢሆንም ነገሩ ልቤን አሞቀው።

ወደቤቴ መሄጃው መንገድ ዳገታማ፣ አስቸጋሪና የሚያንሸራትት ቢሆንም፣ እቤቴ እስከደርስ አመስጋኝነቴና ደስታዬ እንደቀጠለ ነው። የቤቴን መግቢያ በር እንደከፈትኩ ረጂምና አቀበታማ ደረጃ ገጠመኝ። "ደረጃውን እንዴት ልወጣው ነው" ብዬ አሰብኩ። ሊፍት እንዳለ ዞር ዞር ብዬ ብፈልግ፣ የለም። አንድ ከላይ የሚኖር ሰው አይቶኝ ረድቶ ወደላይ አወጣኝ። ቢሆንም፣ የሚረዳኝ ሰው ስለነበር እንዴት እድለኛ ነኝ ብዬ አሰብኩኝ ። አብሮኝ የሚኖረው ሰው ሁሌ ደረጃዎቹን መውጣትና መውረድ ባስፈለገኝ ቁጥር ይረዳኝ ነበር።

አንድ እሁድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ፈልጌ መንገድ እንደጀመርኩኝ አንሸራቶኝ ወደቅሁ። የቀኝ እግሬ አጥንት ስንጠቃ ደረሰበት። ከዚያም ምንም መሄድ አቃተኝ ። ከጥቂት ጊዜ በሃላ ወደ ሌላ ቦታ እንደምዘዋወር ተረዳሁኝ። አዲሱ ቦታ ለከተማ በቅርብ ርቀት የሚገኝ ነበር። ሁኔታው አስደሰተኝ። ሆኖም ወደ ስፍራው እንደደረስኩ የፎቅ አልጋ ገጠመኝ። ላይኛው አልጋ ላይ ልተኛ ነው ማለት ነው። አልጋው ላይ ለመውጣት በመሰላል ልዘልቀው ነው ማለት ነው? ወይ እድሌ ብዬ አሰብኩ።

በተቻለኝ መጠን ጠንካራ ለመሆን ትግሌን ቀጠልኩኝ። ዳሩ ግን ሰውነቴ በድካም አልቆ ነበር። የሚመለከታቸውን ኃላፊዎች ባነጋግርም ምንም ሊረዱኝ አልቻሉም። እንግዲህ ይህ በጥቂቱ በስዊድን ውስጥ ያሉ አካል ጉዳተኞችን ኑሮ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው።

ባንጻሩ በተጎዳው እግሬ ችግር ብቻ አይደለም ያየሁት። መልካም እድሎችንም እንዳይ አድርጎኛል። ተሞክሮዎቹ በውስጤ ሌላ አዲስ የፕሮጀክት ሀሳብ አጭረዋል።

ከአዶልፍ ራትዝካ ጋር በመተባበር ይህን DRW ፕሮጀክት ፈጥረናል። በፕሮጀክቱ አማካይነት እንደኔ ካሉ ሰዎች ጋር በመሆን አካል ጉዳተኛ ስደተኞች የሚገባቸውን የተሻለ ክብር እንዲጎናጸፉ አድረገናል።

## ስልጣን

ሁሉም ሰው ስልጣን አለው ፣ ሆኖም ሁሉም እኩል የሆነ ስልጣን የለውም። ስልጣን አንድ ሰው ሊያገኘው ወይም ሊወስደው የሚችለው ነገር ነው። ስልጣን በተለያዩ ወቅቶችና ስፍራዎች የተለያዩ ትርጉሞች ይኖሩታል። ትንሽ ስልጣን ያለው በሌሎች ብዙ ስልጣን ባላቸው ሰዎች ጥገኛ ስር የመሆን አደጋ ይገጥመዋል። አንድ ህጻን ልጅ በአዋቂዎች እጅ ያለ ጥገኛ ነው። የማህበረሰቡ አወቃቀር ነው እንደ ሁኔታው የተለያዩ የስልጣን ተዋረዶች እንዲኖሩ የሚያደርገው። ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው የተሻለ ትምህርት ፣ የተሻለ ስራና የጤና እንክብካቤ ያገኛሉ።

## የስልጣን ተዋረዶች

አንዳንድ ግሩፖች ከሌሎች ያነሰ ስልጣን አላቸው። ይህም የስልጣን ተዋረድ ተብሎ ይጠራል። ለምሳሌ ጾታን፣ መደብን፣ አካል ጉዳትን ፣ የጾታዊ ግንኙነት አተያይን እና የብሄር ማንነትን ሊመለከት ይችላል። እነዚህ የተለያዩ የስልጣን ተዋረዶች እርስ በርስ ይጋመዳሉ። በተለይም የብዙ ስልጣን አልባ ግሩፖች አባል ለሆነ ሰው ሕይወት እጅግ በጣም ከባድ ትሆንበታለች።

## የስልጣን መዋቅር

በህብረተሰቡ ውስጥ እኩልነት እንዳይኖር የሚያደርጉ መዋቅሮች አሉ። እነዚህም የስልጣን መዋቅሮች በመባል ይታወቃሉ። ዘረኝነት፣ ጾታዊ አድልዎና የአካል ጉዳት ፎቢያ (funkofobi) በነዚህ መዋቅሮች ውስጥ ይመደባሉ። መዋቅሮቹ አንዳንድ ሰዎች የትምህርት መማር እድል ፣ የስፍራና የቤት ማግኘት መብት እንዳይኖራቸው ያደርጋሉ። በሰዎች ጤንነትም ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ። አጭር ትምህርት ያላቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ መጥፎ ስራ ነው ያላቸው። ጥቂት ገንዘብና በህይወታቸውም ላይ ትንሽ ስልጣን ነው ያላቸው ። ብዙ ገንዘብና ስልጣን ካላቸው ሰዎች ይልቅ የሚኖሩበት የሕይወት ዘመን አጭር ነው። የምርምር ጥናቶች ይህንን እውነታ ያሳያሉ[4] ።

## አድልዎ

መዋቅራዊ አድልዎ ፣ ኢፍትሀዊ የሆኑ የህብረተሰቡ አካል የተደረጉ ልምምዶች ናቸው። የሚተገበሩ የአሰራር ህጎች የሰዎችን ልዩ ልዩ ሁኔታዎችና ፍላጎቶች ያላገናዘቡ ናቸው። ለምሳሌ ስለቤተሰቦች መዋሃድ ያሉት የህግ አሰራሮች። ድንጋጌዎቹ እንደሚሉት " ማንም ቤተ ሰቡን ወደስዊድን ለማምጣት የሚፈልግ ግለሰብ የራሱ ስራና መጠለያ እንዲኖረው ያስፈልጋል" ይላል። እነዚህ ህጎች ብዙዎቹ አካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ዳግም ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚገናኙበት እድል እንዳይኖር የሚያደርጉ ህጎች ናቸው። ምክንያቱም ለእነሱ መጠለያና ስራ ማግኘት ከባድ

[4] Sammanställning hälsoläget bland nyanlända, s. 7.

ስለሚሆን ነው። የስዊድን ህብረተሰብ በእነዚህ ነገሮች ሊረዳቸው አይችልም። ስለዚህ መስፈርቱ በአድልዎ የተሞላ ነው።

ሌላው ምሳሌ የኢምግሬሽን ባለስልጣን የሚሰጠው መጠለያ አፓርታማ ነው። ህጉ የሚለው ቤቶች ለሁሉም ሰው የሚስማሙ ናቸው ይላል። ነገር ግን ቤቶቹ ለአካል ጉዳተኛ ስደተኞች ተስማሚ ሆነው እስካልተሰናዱ ድረስ ህጉ አካል ጉዳተኞችን የሚያገል ነው ማለት ነው።

## ቅይጣዊ ትንታኔዎች (Intersektionell analys)

ቅይጥነት የሚለው ቃል ከእንግሊዝኛው "ኢንተርሴክሽን" ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ትርጓሜው የተዳቀለ ወይም የተዛመደ ማለት ነው። የተለያዩ የስልጣን ተዋረዶች መጋመድ ምን ያህል በሰዎች ህይወት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ያሳያል። ለመጀመሪያ ጊዜ ቃሉን የተጠቀሙት በ US አሜሪካ የሚኖሩ ጸረ ዘረኞች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች እንደሚሉት፣ ነጭ የሴቶች መብት አቀንቃኞች (feminister) ስለ ሰዎች ዘርና ጎሳ፣ ጾታዊ እሴት ሆነ እድሜ፣ አካል ጉዳት እንደዚሁም መደብ፣ ይዘነጋሉ ።

ቅይጣዊ እይታ (Intersektion) የስልጣን ትርጉም እንዲገባን ይረዳናል ። ያሉትን የስልጣን መዋቅሮች በማሳየት ሰዎች እንዳሻቸው መኖር እንዳይችሉ እንቅፋት ያስቀምጥባቸዋል።አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ይገልጸዋል።

> - *ከልጆቼ ጋር መገናኘት አልችልም፣ በሌላ አገር በስደተኞች ካምፕ ውስጥ ነው ያሉት ። የኢሚግሬሽን ባለስልጣን ቀለባቸውን የመቻል አቅም ስለሌለኝ የመኖሪያ ፈቃድ እንዳላገኝ አሉታዊ መልስ ሰጥቶኛል። እንዴት አርጌ ነው ይህን መስፈርት የማሟላው ለአካል ጉዳቴ የተመቻቸ ስራ ሳይፈጥሩልኝ? እንደዚሁም፣ ከልጆቼ ጋር መሆን አለመቻሌ ለቁዘማና ለድብርት ነው የዳረገኝ " ።*

ጥናት[5] እንደሚያሳየው ሴቶች ስደተኞች ከሌሎች ይልቅ በከባድ ኑሮ ውስጥ ያልፋሉ። ከወንዶች ይልቅ ስራ ማግኘት ይከብዳቸዋል። አካል ጉዳተኞችም እንደዚሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያልፋሉ ። በስራ ገበያው ፉክክር[6] በጣም አናሳ እድሎች ነው ያላቸው።

ከዚህ በላይ ያለውን ገጠመኝ የነገረችን ሰው አካል ጉዳት ያላት ሴት ስደተኛ ነች። እነዚህ ሁሉ ነገሮች አንድ ላይ በማበር ስራቸውን ይሰራሉ። የዚህም ውጤት ከልጆቿ ጋር እንዳትገናኝ ያደርጋታል። ቅይጣዊ አተያይ (intersektionellt perspektiv) ለዲሞክራሲ፣ ለፍትህና ለእኩልነት አስፈላጊ ነው።

---

[5] Riksrevisionens rapport om jämställdhetsintegrering av integrationspolitiken skr. 20181997, s. 5
[6]Situationen på arbetsmarknaden för personer med funktionsnedsättning 2017, s. 8 7 https://www.ohchr.org/EN/HRBodies/CRPD/Pages/Conven- tionRightsPersonsWithDisabilities.aspx

## ሁለንተናዊ ተሳትፎ - አሳታፊ ስርዓት ለሁሉ ።

ኢንተግሬሽን የሚለው ቃል ትናንሽ ክፍለ አካላትን በማገጣጠም አንድ ሙሉ አካል መፍጠር ማለት ነው ። የትኛውም ክፍለ አካል ከሌሎቹ የበለጠ ስልጣን አይኖረውም ። በዚህ መንገድ ይሄ ቃል ጥሩ ነው።

ስዊድን ሁለንተናዊ ነች። ስዊድን የተለያዩ ባህሎች ውጤት ነች። ማንም ከሌላው የበለጠ ስልጣን ሊኖረው አይገባም። ነገር ግን ሁሉ አካታች ስርአት፣ የአካል ጉዳተኛ ስደተኞች ህይወት እንዴት እንደሆነ መረዳትን ይጠይቃል።

ከባዱ ነገር ፖለቲካ ሁልጊዜ ርካሽ ወጪ የሚጠይቀውን አማራጭ እንደ መፍትሄ ሲቆጥር ነው። ይልቁኑ ፖለቲካ ማለት ዲሞክራሲ፣ እኩልነትና የሰው ፍጥረት ክቡርነት ነው።

የጥገኝነት ማመልከቻው መታየት ከመጀመሩ በፊት፣ ጉዳዩ በሚጠናበት ጊዜና ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ስዊድን እንዴት አርጋ አካል ጉዳተኛ ስደተኞችን በተሻለ መንገድ ማስተናገድ እንደሚገባት ማሰብ አለብን።

ነገሩ ብዙ ነገሮችን ያካትታል፣ ምቹ የጉዞ አገልግሎትን (f'ärdtjänst) ጥሩ የቋንቋ ትምህርትን (SFI)፣ ጥሩ የጤና አገልግሎትን፣ እኩል አሳታፊ የስራ እድልን ፣ ትምህርት ቤቶችንና የድጋፍ አስተዋፅዎን ይጠይቃል። እነዚህ ነገሮች በተሟሉበት መጠን፣ አካል ጉዳተኛ ስደተኞችም ለሌሎች ዜጎች የተቀመጡት መስፈርቶች ሁሉ እነሱንም በእኩልነት ይመለከታቸዋል።

የተሳካና ሁሉን አካታች ስርአት እንዲኖር ህብረተሰቡ ሁሉ ሰው ራሱን ችሎ መኖር እንዲችል ማድረግ አለበት ። ፖለቲካው ፣ አካል ጉዳተኛ ስደተኞችን የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ድጋፍ በመስጠት የማህበረሰቡ አካል ማድረግ ይጠበቅበታል። ያኔ ማህበረሰቡ የሚጠይቃቸውን ነገሮች እነሱም በተራቸው ያሟላሉ።

ከነልዩነታችን በመከባበር እርስ በርስ መገናኘታችን አስፈላጊ ነው። ልዩነት አንዱ የስዊድን ማህበረሰብ ማንነት አካል ነው።




BEVILJAT

# 2. ስደትና መብቶች በስዊድን

## አስፈላጊ ቃላት ከነፍቻቸው።

በየጊዜው አካል ጉዳተኞች የሚገለጡበት ብዙ ልዩ ልዩ ቃላት አሉ። ብዙዎቹን በዚህ ዘመን አንጠቀማቸውም ። ድኩም ፣ ደደብ እና አዕምሮ ቢስ የሚሉ ያረጁና ጸያፍነት ያላቸው ቃላት ምሳሌዎች ናቸው።

ባሁኑ ጊዜ በአብዛኛው በጥቅም ላይ ያሉት ቃላት  አካል ጉዳት እና ግድብ የአካል ብቃት (funktionsnedsättning och funktionshinder) የሚሉት ናቸው። ሆኖም አለምና ወቅቱ በእድገት ሂደት ላይ እንደመሆናቸው፣ ብዙዎቹ "የተለያየ አቅመ ክህሎት ያላቸው" የሚለውን ቃል መጠቀም ይቀናቸዋል።

የአካል ጉዳት እንቅስቃሴ አራማጆችና ከአካል ጉዳት ጋር የሚሰሩ ደርጅቶች የትኛው ቃል ከሁሉ እንደሚሻል እስካሁን ሊስማሙ አልቻሉም። አስፈላጊው ነገር እያንዳንዳቸው የትኛው ቃል በይበልጥ እንደሚገልጻቸው ራሳቸው መርጠው መጠቀም መቻላቸው ነው።

DRW ፣ "normbrytande funktionalitet" ከተለመደው ያፈነገጠ የአካል ብቃት ጉድለት የሚለውን አገላለጽ እንጠቀማለን። ይህንን የምናደርገው ስህተቱ በግለሰቡ ምክንያት አለመሆኑን ለማሳየት ነው። ስህተቱ በማህበረሰቡ ባሉ ኖርሞችና መዋቅሮች ምክንያት ብቻ የመጣ ስለሆነ ነው።

### ስደተኛ (Migrant)

ስደተኛ፣ የአንድን አገር ድንበር ተሻግሮ በመምጣት ኑሮውን በዚያ መመስረት የሚፈልግ ሰው ነው። ሁኔታዎቹ በብዙ የተለያዩ ምክንያቶች ሊመጡ ይችላሉ።

በፍልሰት የመጣ ስደተኛ ፣ በጦርነት፣ በአመጸ ወይም በመሳደድ ቤቱን ትቶ የሸሸ ሰው ነው። ስደተኞች ሁሉ ጥገኞች አይደሉም።

### *መቋቋም* (Etablering)

ፖለቲከኞችና ባለስልጣኖች ብዙ ጊዜ ስለ መቋቋም ያወራሉ። ይህም አንድ ሰው በስዊድን ውስጥ እንዲቆይ ፈቃድ ካገኘ በሃላ ያለው ጊዜ ነው።

ለመጀመሪያዎቹ ሁለት አመታት የተዘረጋ ልዩ የእቅድ መርሀ ግብር አለ። በዚህ ጊዜ ሰዎች ስዊድን ውስጥ ኑሮ መመስረት እንዲችሉ ልዩ ተጨማሪ ድጋፍ ያገኛሉ። ስራ እንዲያገኙ ወይም ትምህርት እንዲጀምሩ ድጋፍ ይሰጣቸዋል። እንደማንኛውም የማህብረሰቡ አካል ይቆጠራሉ። ይህም በፖለቲከኞቹ ውሳኔ የጸና ነው።

## አካል ጉዳት (Funktionshinder)

ማህበረሰቡ ሰው ሁሉ ተሳታፊ መሆን እንዲችል እንቅፋቶችን ማስወገድ አለበት። እንደ ደረጃዎች ያሉና ሌሎች የግንባታ እንቅፋቶችን ይመለከታል። እንዲሁም ሌሎች ለመረዳት የሚከብዱ መረጃዎችንም ይመለከታል።

ብዙ የተለያዩ ነገሮች ለሰዎች እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ። በመንገድ ላይ የአንድን ሰው እንቅስቃሴ የሚያደናቅፉ ነገሮች ብቻ ሳይሆኑ፣ ለመረዳት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችንም ሊመለከት ይችላል።

ማህበረሰቡ እኮ ነው እንቅፋት ፈጣሪው። ስለ አካል ጉዳት ስንናገር ማህበረሰቡን ነው በኃላፊነት የምንጠይቀው ። ጥያቄው ሰብአዊ መብቶችን ይመለከታል። ማንም ሰው ተሳታፊ እንዲሆን የማያግድ ከባቢዎች መፍጠር አለብን።

ለበለጠ መረጃ የአካል ጉዳተኛ መብቶች ውልን[7] ማንበብ ይቻላል። በማንም ሰው ላይ በር የማይዘጋ ማህበረሰብ በተሻለ መንገድ ይሰራል። ስለዚህ ጥሩ እቅዶችን ማውጣት ይገባናል። በህግና በፖለቲካ ውስጥ አካል ጉዳት የሚለው አስፈላጊ ቃል ነው። ለምሳሌ ቤቶችና ከተማዎች እንዴት እንደሚገነቡ የሚደነግጉ የተለዩ ህጎች አሉ።

## አካላዊ ዝንፈት (Funktionsvariation)

ሁሉም ሰው አንድ፣ የሆነ የአካል ብቃት ጉድለት አለበት። ሰውነቶቻችን በተለያዩ መንገዶች ስራቸውን ይሠራሉ። እንደዚሁም፣ የትኛው አካል  ነው በትክክል መንገድ የሚሰራው በሚለው ዙሪያ አንድ ሀሳብ አለ። ብዙዎቹ የአካል ዝንፈት (funktionsvariation) የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት ከተለመደው አካል ብቃት ወይም አካል ጉድለት (normbrytande funktionalitet) ያፈነገጠ ለማለት ሲፈልጉ ነው።

ነገር ግን አካላዊ ዝንፈት ከዚያም የላቀ ትርጉም አለው። አካል ጉዳት ቢኖርበትም ባይኖርበትም እንዴት ያ ሰው ተግባሩን እንደሚያከናውን የሚገልጽ ነው።

## ከተለመደው ያፈነገጠ አካል ብቃት (Normbrytande funktionalitet)

ኖርማል ተብሎ የሚታሰብ ነገር በጊዜ ሂደት ይቀያየራል። ብዙ ጊዜ ማህበረሰቡን የምንቀርፀው በጊዜው  ኖርማል ብለን ከምናስበው ነገር በመነሳት ነው። ስለዚህ ሌላ የአካል ጉዳት ሲኖር የበለጠ ከባድ ይሆናል።

ሰዎች ሁሉ በተለያየ መንገድ ይሠራሉ። አንድ ሰው አካሉ ከሌሎቹ በተለየ ሲሰራ ፣ያ ሰው ከተለመደው ኖርም አፈነገጠ ማለት ነው። ያ ሰው ስህተት ነው ማለት አይደለም።

ባጭሩ፣ ከተለመደው የአካል ብቃት ባፈነገጠ አሰራር፣ ሌሎች ሰዎች ኖርማል ብለው ከሚያዩት በተለየ መንገድ የሚሰራ አካል ነው። DRW ፣ በኖርምና ከኖርሙ ባፈነገጡ የአካል አሰራር ዙሪያ በደስታ ማውራት ይፈልጋል።

---

[7] https://www.ohchr.org/EN/HRBodies/CRPD/Pages/Conven- tionRightsPersonsWithDisabilities.aspx

የትኞቹ ልማዳዊ አተያዮች አንዳንድ ሰዎች ተሳታፊ ሚና እንዳይኖራቸው በር የሚዘጉ እንዳሉ ማሳየት እንፈልጋለን። DRW፣ አካል ጉዳትን እንዴት እንደምናይ በማህበረሰባችን ውስጥ ያለውን አተያይ መቀየር ይፈልጋል።

## ተደራሽነት (Tillgänglighet)

ተደራሽነት አንድ መብት ነው። ማህበረሰቡን ሁሉ ሰው ሊሰተናግድ በሚችልበት መንገድ መገንባት ይኖርብናል። ኩባንያዎች፣ መንግስት፣ ክፍለ ህገራት እና የወረዳ መስተዳደሮች፣ ሁሉ ለዚህ ሀላፊነት አለባቸው።

ለምሳሌ እነዚህ ሀሳቦች ትኩረት ማግኘት ይኖርባቸዋል፤ ቤቶች ስንሰራ እንዴት ነው፣ አስፈላጊ መረጃዎችን እንዴት እንናገራለን ፣ እንደዚሁም የትኛውን እርዳታና ድጋፍ ሰዎች ያገኛሉ። ስዊድን ውስጥ ስለተደራሽነት ግድ አለመስጠት ወንጀል ነው። አድልዎ መፍጠር ነው የሚሆነው።

ማህበረሰቡ የተመቻቸና የበለጠ ተደራሽ መሆን ይገባዋል። ሆኖም ግን አንዳንድ ሰዎች መቼም ቢሆን ልዩ እርዳታና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ይህን ማስታወስ ግድ ይሏል።

## ሰብአዊ መብቶች

ሰብአዊ መብቶች ሁሉን ሰዎች ይመለከታሉ። ሁላችንም ነጻ ሆነን ተወልደናል፣ ከአንድ አይነት ክብርና ከእኩል መብትም ጭምር ጋር ። ባለስልጣኖች የሰብአዊ መብት መከበርን የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው። ይህም በተለያዩ ህጎች ላይ ተቀምጧል።

## አስፈላጊ ህጎች በስዊድን

ስዊድን ውስጥ አንዳንድ ልዩ የሆኑ አስፈላጊ ህጎች አሉ። ህገ መንግስት (grundlager) ተብለው ይጠራሉ። በነዚህ ህጎች ላይ ማህበረሰቡ እንዴት መመራት እንዳለበት ተቀምጧል። እንደዚሁም የትኞቹ መብቶች እንዳሉን የተቀመጠበት ሌሎች በዛ ያሉ ህጎች አሉ። ባለስልጣኖቹ ህጎቹን መከተል አለባቸው።

የአውሮፓ ህብረትም (EU) ብዙ አስፈላጊ ህጎች አሉት ። EU ፣ ከለላ የመጠየቅ መብትና ቤተሰቦች አንድ ላይ መኖር እንዲችሉ የሚፈቅዱ ህጎች አሉት ።

በ EU ውስጥ ያሉ ህጎች በተመሳሳይ መንገድ በስዊድንም ውስጥ ልክ እንደ አገሪቷ ህጎች ይሠራሉ። እንደዚሁም በ EU ውስጥ አንድ ልዩ ፍርድ ቤት አለ።

## ምቹ ዋስትና (Välfärden)

ምቹ ዋስትና በስዊድን ማህበረሰብ ዋና አስፈላጊ ክፍል ነው። ይኸው መብት ላለፉት መቶ አመታት በዚህ አይነት መንገድ ሲተገበር ቆይቷል።

ይህም ማለት ፣ ማህበረሰቡ ለነዋሪዎች አስተማማኝ ኑሮ እንዲኖሩ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠትን ይመለከታል። ሁሉ ሰው ቀረጥ የመክፈል ግዴታ አለበት። ገንዘቦቹ የምቹ ዋስትናውን ወጪዎች ይሸፍናሉ። ስራና የስራ ገበያን በሚመለከት መንግስት ብዙ የሚወስነው ነገር የለም። የሰራተኞች ማህበራትና አሰሪዎች ናቸው የሚስማሙት።

ነገር ግን ሌሎች ነገሮችን በሚመለከት መንግስት ብዙ ስልጣን አለው። ለምሳሌ ትምህርትንና ጤና ጥበቃን በሚመለከት ። በስዊድን አንዱ አስፈላጊ ክፍል ምቹ ዋስትና የአካል ጉዳትን የሚመለከተው ፖለቲካ ነው።

## LSS አስፈላጊ ህግ ነው።

LSS ማለት ለአንዳንድ አካል ጉዳተኛ ድጋፍ አገልግሎትን የሚሰጥ ህግ ነው። ይሄ ህግ ለምሳሌ አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የግል ረዳት እንዲያገኙ መብት ይሰጣል።

በስዊድን ውስጥ የሚኖሩ ሁሉ ተመሳሳይ ድጋፍ የማግኘት መብት የላቸውም። አንዳንድ እርዳታ ግለሰቡ ዜጋ ከሆነና ይኸው ሰው ቀደም ብሎ ሥራ ከሠራ የሚሰጥ ነው። የመድህን ድርጅት (Försäkringskassan) አንድ ሰው እርዳታ የማግኘት መብት እንዳለው ይመረምራል። ይሄ የሚያሳየው የሚኖሩንን መብቶች በሚመለከት አንዳንድ ልዩነቶች እንዳሉ ነው።

## ፍርድ ቤቶች (Domstolarna)

በስዊድን ውስጥ ብዙ ልዩ ልዩ ፍርድ ቤቶች አሉ። ራሳቸውን የቻሉ ናቸው። ፖለቲከኞች በላያቸው ላይ የማዘዝ ስልጣን የላቸውም። አንድ ሰው፣ አንድ ባለስልጣን በፍርድ ቤት የወሰነውን ውሳኔ፣ ይግባኝ ማለት ይችላል። ለምሳሌ የስደተኞች ባለስልጣን (Migrationsverket ) የሚወስነውን ውሳኔ።

ያንን ለማድረግ ምንም ተጨማሪ ወጪ አይጠይቅም። ነገር ግን ባለጉዳዩ የህግ አዋቂ እርዳታ ሊያስፈልገው ይችላል። ብዙ ጊዜ ግለሰቡ ራሱ ወጪውን መሸፈን ይኖርበታል።

በሌላ አነጋገር በባለስልጣኖችና ይግባኝ ለማለት በሚፈልገው ግለሰብ መካከል እኩልነት የለም ማለት ነው።

አንድ ህግ የተለያየ አተረጓጎም የሚኖረው ከሆነ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ይጣራል። ፍርድ ቤቶቹ ባለስልጣኖች እንዴት ህጉን መጠቀም እንዳለባቸው ይወስናሉ።

## የተባበሩት መንግስታት (Förenta Nationerna - FN)

ስዊድን ፣የተባበሩት መንግስታት የአካል ጉዳተኛ ሰዎችን መብቶች ስምምነት ለማክበር ቃል ገብታለች። እንደ እውነቱ ከሆነ ስምምነቱ ሌላ አዲስ መብቶችን አይደለም የሚመለከተው።

ዋናው ነገር የተለመዱት ሰብአዊ መብቶች አካል ጉዳተኞችንም ማቀፍ መቻላቸው ነው። በተባበሩት መንግስታት ውስጥ አገሮች ህጎቹን እንደሚያከብሩ የሚቆጣጠር አንድ ቡድን አለ። ይሄ ቡድን በ 2014 ዓ.ም. በስዊድን ላይ ወቀሳ ሰንዝሯል። እንደ ቡድኑ አባባል ፣ ስዊድን ለግለሰብ ረዳቶች ለሚወጣው ወጪ በቂ ገንዘብ መመደብ ይጠበቅባታል። እንዲሁም ተደራሽነትን ከመጤፍ የማይቆጥሩ አንድ ፣ የሆነ አይነት ቅጣት ሊጣልባቸው ይገባል።

## የአውሮፓ ስምምነት (Europakonventionen)

በ 1952 ዓ.ም. ስዊድን የአውሮፓ ስምምነትን ፈረመች። በ1995 ዓ.ም. የስዊድን ህግ ሆነ። ማናቸውም አይነት አዲስ ህጎች ይህን ህግ መቃወም አይችሉም።

ብዙዎቹ በአውሮፓ ስምምነት ውስጥ ያሉ ደንቦች ለስደተኞች አስፈላጊ ናቸው። ለምሳሌ ሰው ሁሉ ከቤተሰቡ ጋር የመሆን መብት አለው የሚለው ደንብ። በጦርነት ምክንያት የተለያዩ ቤተሰቦች እንደገና አብረው የመሆን መብት አላቸው።

ደንቦቹ በአውሮፓ ስምምነት እንዴት እንደሚሰሩ ሁሌ ግልጽ አይደሉም። በየጊዜው እድገት የሚያሳይ አንድ ነገር ይኖራል።

## **ልዩ ልዩ የመኖሪያ ፈቃዶች**

በዚህ ክፍል ስለ ተለያዩ የመኖሪያ ፈቃድ አይነቶችና እንደዚሁም እንዴት ስዊድን ስደተኞችን እንደምትቀበል ጭምር እናወራለን።

የስደት ፖለቲካ በየጊዜው ይለዋወጣል። ልክ በአሁኑ ጊዜ በስራ ላይ ያሉ ህጎች ምን ይመስላሉ የሚለውን አጣርቶ ማየት አስፈላጊ ይሆናል።

## ስደተኞች (Migranter)

ልዩ ልዩ ለሆኑት የስደተኞች ግሩፖች የተለያዩ ህጎችና ደንቦች አሏቸው። ሁሉም በስዊድን ውስጥ የመቆየት እኩል መብት አይኖራቸውም።

አንድ ሰው ስዊድን ውስጥ የጥገኝነት ጥያቄ ካቀረበ ይህ ሰው ከለላ ፈላጊ ተብሎ ይጠራል።ባለስልጣኖቹ ይሄ ሰው የከለላ መብት አለው ብለው ካሰቡ ጥገኛ (flykting) ብለው ይጠሩታል። የጥገኛ ቤተሰቦችም ወደ ስዊድን የመምጣት መብት ይኖራቸዋል። ባላቸው ዝምድና አማካይነት የመኖሪያ ፈቃድ ማመልከት ይችላሉ።

ከዚያም ጥገኛውና ቤተሰቡ አንድ ላይ እንደ አዲስ መጦች ይቆጠራሉ። በስዊድን ውስጥ ልዩ የሆነ ድጋፍና እርዳታ ይሰጣቸዋል። በዚያ ፈንታ አንድ ሰው ወደ ስዊድን ለጉብኝት መምጣት ቢፈልግ የቱሪስት ቪዛ ሊያገኝ ይችላል። ከዚያም ይሄ ሰው ለ90 ቀናት ስዊድን ውስጥ መቆየት ይፈቀድለታል።

እንዲሁም አንድ ሰው በስራ ምክንያት ፣ በትምህርትና በሌሎችም ምክንያቶች የመኖሪያ ፈቃድ ሊያመለክት ይችላል።

ይህም በውጪ ሀገር ሰዎች ህግ (utlänningslagen) ላይ ይገኛል። እንደዚሁም በ2016 ዓ.ም የወጣ አንድ ጊዜያዊ ህግ አለ። በዚያ ህግ መሠረት ወደ ስዊድን ለመምጣት፣ ፈቃድ ለማግኘት፣ በጣም ጠንከር ያሉ ደንቦች ተቀምጠዋል።

## ከለላ ፈላጊ (Asylsökande)

ስዊድን ውስጥ ከለላ ፈላጊ ሰዎች ፣ወደ አገሪቱ ለጉብኝት ብቻ ከሚመጣው ሰው ይልቅ ሌሎች መብቶች አላቸው። በአገሪቱ የመሆን መብት አላቸው። እንደዚሁም መኖሪያ ቤት የማግኘት መብት፣ የጤና ጥበቃና የገንዘብ ድጋፍም ጭምር።

## ስደተኛ  (Flykting)

ማን ማን እንደ ስደተኛ ሊቆጠር እንደሚችል የሚደነግጉ የተለዩ ደንቦች አሉ ። እነዚህም በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ስምምነት ውስጥ ተቀምጠዋል።

አንድ ሰው ስደተኛ ለመሆን ፣ ሰውየው የመሳደድ ፍራቻውን በምክንያት ማሳየት መቻል አለበት።ግለሰቡን ብቻ ሊመለከት ይገባዋል። ነገሩ በራስህ/በራስሽ የደረሰ ችግር መሆን አለበት እንጂ ከጦርነትና ከቦንብ መሸሽ ጋር አንድ አይነት ነገር አይደለም ።

በድሮ ጊዜ፣ አንድ ሰው በየትኛው ምክንያት ስዊድን ውስጥ ከለላ ማግኘቱ ብዙ ለውጥ አልነበረውም። ለሁሉ ተመሳሳይ ደንቦች ነበራቸው። ነገር ግን ከ2016 ጀምሮ፣ የትኞቹ እንደ ስደተኞች እንደሚቆጠሩ፣ የትኞቹ ደግሞ

ከለላ እንደሚያስፈልጋቸው የተለያዩ ህጎች አሉ ። አንድ ሰው እንደ ስደተኛ የሚቆጠር ከሆነ በቅድሚያ ለሦስት አመት የሚያገለግል ፈቃድ ያገኛል። ሦስቱ አመታት ሲያልፉ ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል።

## አማራጭ ከለላ ፈላጊዎች (Alternativt skyddsbehövande)

ሰው የገዛ አገሩን ጥሎ እንዲሸሽ የሚያደርጉ ብዙ ምክንያቶች ይኖራሉ። ሰዎች ከጦርነት፣ ከአመጻና ከአደጋ ስጋት ሊሸሹ ይችላሉ። በስዊድን ህጎች አማራጭ ከለላ ፈላጊ ተብሎ ይጠራል። አንድ ሰው አማራጭ ከለላ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ መጀመሪያ ለአስራ ሦስት ወራት መቆየት የሚያስችል ፈቃድ ያገኛል። በቀጣይነት ከለላ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ አዲስ ማመልከቻ ማስገባት ይኖርበታል።

## ልዩ ትኩረት ሳቢ ሁኔታዎች

በቀደሙት አመታት ብዙዎች በበሽታዎችና በአካል ጉዳት ምክንያት ስዊድን ውስጥ ለመቆየት ፈቃድ ያገኙ ነበር።

እንደዚሁም አንድ ሰው ስዊድን ውስጥ ለረጂም ጊዜ ከመቆየቱ የተነሳ በገዛ አገሩ መኖር በጣም የሚከብደው ከሆነ የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘት ይችል ነበር።

ይሄ፣ አስተያየት በማድረግ ወይም በጤና ምክንያት፣ተብሎ ይጠራ ነበር። ከ2016 ጀምሮ ህጎቹ የበለጠ ጠበቅ ብለዋል። ባሁኑ ጊዜ በአብዛኛው ማንም በነዚህ ምክንያቶች የመኖሪያ ፈቃድ የሚያገኝ የለም።

አንድ ሰው ከመታመሙ የተነሳ ከስዊድን መውጣት ባይችል እንደዚያ አይነት የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል። ነገር ግን ሁኔታው ለሞት የሚያሰጋው ከሆነ ብቻ ነው።

### አዲስ መጥ (Nyanländ)

አዲስ የመጣ ሰው ማለት በቀላሉ ለስዊድን አገር አዲስ የሆነ ሰው ማለት ነው። ነገር ግን የስዊድን ባለስልጣኖች ቃሉን በሌላ መንገድ ይጠቀሙታል።

ባለስልጣኖቹ ቃሉን ስዊድን ውስጥ የጥገኝነት ፈቃድ ላገኙ ሰዎች ይጠቀሙበታል። እንደ አዲስ መጥ የሚቆጠሩት የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙበት ጊዜ አንስቶ ለመጀመሪያዎቹ ሁለት አመታት ነው።

### ወረቀት አልባ (Papperslös)

በስዊድን ውስጥ መሆን መብት የሌለው ሰው ወረቀት አልባ ተብሎ ይጠራል። በአብዛኛው ጥገኝነት አመልክተው አይሆንም የተባሉ ሰዎችና ወደ አገራቸው መመለስ የማይፈልጉ ወይም የማይችሉ ሰዎች ናቸው ።

## ስራ ወይም ትምህርት

አንድ ሰው ለመስራት ወይም ለመማር የመኖሪያ ፈቃድ ሊያገኝ ይችላል። ይህ አይነቱን ፈቃድ ብዙ ጊዜ ከአገሩ ሆኖ ነው ማመልከት ያለበት ።

ጥገኝነት ያመለከተ ሰው አንዳንዴ ቀጥታ ስዊድን ውስጥ ሆኖ ለስራ ወይም ለትምህርት ፈቃድ ማመልከት ይችላል።

በ2017 እና በ 2018 ዓ.ም. 2ኛ ደረጃ ትምህርት ስለመማር አንድ ህግ ወጣ። በስዊድን ውስጥ ለመኖር ጥገኝነት ያመለከቱ ወጣቶች የ 2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እስኪጨርሱ መቆየት እንዲችሉ የሚፈቅድ ህግ ነው።

ፖለቲከኞቹ ይህንን አዲስ ህግ በጣም በፍጥነት ስለሰሩት ፤ ህጉን ለመረዳት ከባድ ሆኖ ነበር። ህጉን በስራ ለመተግበርም ከባድ ሆኖ ቆይቷል ።

## ቤተሰብ በስዊድን

ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር የመኖር መብት አላቸው። አንድ ሰው ስዊድን ውስጥ የመኖር ከለላ ካገኘ የገዛ ቤተሰቦቹ በኋላ ተከትለው የመምጣት መብት አላቸው።

ነገር ግን እንደዚህ የሚል ደንብ አለ፤ የራሱን ቤተሰብ እዚህ ለማምጣት የሚፈልግ ሰው፣ ስራና መጠነኛ ቤት እንዲኖረው ያስፈልጋል። እነዚህ ደንቦች ብዙ ቤተሰቦች አብረው እንዳይኖሩ እንቅፋት ይሆናሉ።

አካል ጉዳት ላለበት ሰው ደግሞ ከዚያም በከፋ ከባድ ይሆናል። ለብዙዎቹ ስዊድን ውስጥ ስራ ማግኘት ሊሆን የማይችል ነገር ነው። ታዲያ ያኔ እንደገና ከቤተሰባቸው ጋር መገናኘት የማይቻል ነገር ነው።

DRW ለዚህ ግሩፕ የሚመጥን ልዩ የሆኑ ደንቦች እንዲኖር ያሳስባል። አለበለዚያ ግን ስዊድን ሰብአዊ መብቶችን እየጣሰች ነው ማለት ነው። አዲስ ህጎችንና ደንቦችን የሚያረቁ፣ ሁልጊዜ አካል ጉዳት ጥያቄዎችንና አመለካከቶችን ታሳቢ ቢያደርጉ መልካም ይሆናል።

## ተመልሶ መሄድ

አንድ ሰው ስዊድን ውስጥ የመቆየት ፈቃድ ካላገኘ ከሀገር እንዲወጣ ውሳኔ ሊተላለፍበት ይችላል። እንደዚሁም ግለሰቡ ለተወሰነ ጊዜ ወደ ስዊድን ተመልሶ መግባት እንዳይችል ሊከለከል ይችላል። አንዳንዴ አንድ ግለሰብ ከአገር እስኪወጣ ድረስ በፖሊስና በስደተኞች ባለስልጣን በቁጥጥር ስር ሊውል ይችላል ፤ በማቆያ ስፍራ ይጠበቃል።

አንድ ሰው በሌላ EU ውስጥ ባለ አገር ጥገኝነት ካመለከተ ስዊድን ውስጥ ከለላ እንዲያገኝ ለማመልከት ለተወሰነ ጊዜ መቆየት አለበት። ይህም በዱብሊን ህገ ድንጋጌ ላይ ተቀምጧል። በስዊድን ውስጥ የመቆየት ፈቃድ ያላገኙ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ቀጣይ እድል ፈንታ ምን እንደሆነ እምብዛም አናውቅም።

## መስተንግዶና መቋቋም

ጥገኞችና ሌሎችም በስዊድን የሚኖሩ ከለላ ፈላጊዎች፣ መጠነ ሰፊ እርዳታ ያገኛሉ። ለሌሎች ስደተኛ ቡድኖች ግን እንደዚያ አይደለም።

ስዊድን ውስጥ ከለላ የሚያስፈልጋቸው ህዝቦች መጠነኛ የገንዘብ እርዳታና የመኖሪያ ቤት ይሰጣቸዋል።ይህንንም የሚያመቻቸው የስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን ነው። ለጥገኝነት ያመለከቱ ሰዎች የመኖሪያ ፈቃድ ሲያገኙ በስራ ስምሪት ባለስልጣን (Arbetsförmedlingen) አማካይነት ይረዳሉ። ይህም የመቋቋሚያ መርሀ ግብር ተብሎ ይጠራል።

ስዊድንኛ ቋንቋ ይማራሉ፣ ስለ ስዊድን እውቀት ይገበያሉ፣ እንዲሁም የስራ ልምምድ ያደርጋሉ። ስራ እንዲያገኙ እርዳታ ይሰጣቸዋል፣ ስዊድንኛ ቋንቋ እንዲማሩና የራሳቸውን ቢዝነስ ለመጀመሪያ ድጎማ ያገኛሉ። ወደ ስዊድን የሚመጡ ሁሉ ይህንን መብት አያገኙም። ለምሳሌ ከትዳር ጓደኛቸው ጋር ለመቀላቀል የሚመጡትን በሚመለከት ፣ ኑሮአቸውን በሰዊድን ውስጥ መጀመር በጣም ሊከብዳቸው ይችላል። ለነሱ ማን ድጋፍና እርዳታ እንደሚሰጣቸው ግልጽ ነገር የለም።

## አካል ጉዳት ያላቸው ስደተኞች (Migranter med normbrytande funktionalitet)

የስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን ነው ማን ስዊድን ውስጥ መኖር እንደሚፈቀድለት የሚወስነው። ግለሰቦች ውሳኔያቸውን ለልዩ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላሉ። ግለሰቦቹ ስዊድን ውስጥ ለመኖር እንደሚችሉና እንደማይችሉ ለማወቅ ብዙ አመታት ሊወስድ ይችላል። የአካል ጉዳት ያላቸው ስደተኞች ፈቃዳቸውን በሚጠባበቁበት ወቅት ልዩ እርዳታ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። የትኞቹ መብቶች እንዳላቸው በተለያዩ ህጎች ላይ ተቀምጧል።

LSS የተባለው ህግ አንድ አንድ የአካል ጉዳት ላላቸው ሰዎች ተጨማሪ ድጋፍ ይሰጣል። ለምሳሌ በግል ረዳት አማካይነት። ትልቁ ችግር ይሄ LSS ህግ የመኖሪያ ፈቃድ አመልካቾችን አይመለከትም። ከስደተኞች ባለስልጣን መልስ እየተጠባበቁ ሳሉ የሚያገኙት አንዳች ድጋፍ የለም ማለት ነው።

ለብዙዎቹ የእንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው የጉዞ አገልግሎት (färdtjänst) አስፈላጊ ድጋፍ ነው። የወረዳና የአውራጃ መስተዳደሮች ናቸው ፈቃድ የሚሰጡት። ለከለላ አመልካቾች የጉዞ አገልግሎት መብት መስጠቱ የነዚህ ባለስልጣኖች ምርጫ ነው። ነገር ግን መስጠት አለባቸው የሚል ህግ የለም።

## የራስን እድል መወሰን

ሁሉ ሰው የማህበረሰቡ አካል የመሆን መብት አለው። ሁሉም በገዛ ህይወቱ ላይ የመወሰን መብት አለው። ይህም በብዙ ህጎች ላይ ተቀምጧል። ህጎቹ ከብዙ ሰዎች ተጋድሎ በኋላ የመጡ ናቸው።ፖለቲከኞቹም ሰምተዋቸዋል።

## ማህበራዊ አገልግሎት ህግ (Socialtjänstlagen)

ማህበራዊ አገልግሎት ህግ የገንዘብ እርዳታንና በሚኖሩበት ስፍራ የሚገኝ እርዳታን ይመለከታል ። ወረዳዎች በቀበሌያቸው ውስጥ የሚኖሩትን ሁሉ መርዳት አለባቸው። በወረዳው ያለው ማህበራዊ አገልግሎት በከባድ ኑሮ ጫና ውስጥ ያሉ ሰዎችን መርዳት አለበት።ወረዳው ሰዎች በእየለቱ አንድ የስራ እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው ያደርጋል። በሚስማማቸው መንገድ መኖር እንዲችሉ ያመቻቻል፤ የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ በመስጠት ይረዳቸዋል። ወረዳው እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ልዩ አገልግሎት የሚሰጡ ቤቶችና አፓርታማዎች ያዘጋጃል።

በወረዳው አስተዳደር ውስጥ ያሉት ፖለቲከኞች ናቸው የማህበራዊው አገልግሎት እንዴት እንደሚሰራ የሚወስኑት። አንድ ሰው በማህበራዊ ጉዳይ አገልግሎት እርዳታ ከፈለገ ወደ ቢሮአቸው ይሄዳል። እዚያም፣ የሚፈልገውን እርዳታ ይናገራል። ከዚያም አንድ በቢሮ የሚሰራ ሰው መጥቶ የትኛው እርዳታ ሊሰጠው እንደሚችል ያጣራል።

## LSS በመባል የሚታወቀው ህግ

LSS ህግ ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች ታስቦ የተቋቋመ ህግ ነው። በተቻለ መጠን ጥሩ ኑሮ መኖር እንዲችሉ እርዳታ ያገኛሉ። ስራ እንዲሰሩ፣ ትምህርት እንዲማሩ ወይም ማናቸውንም ለነሱ ትርጉም የሚሰጥ ተግባር በየቀኑ እንዲሰሩ ይፈቀድላቸዋል። እንደዚሁም ቲአትርና ኮንሰርት እንዲገቡ ፣ ስፖርትና ማንኛውንም የሚወዱትን ነገር ማድረግ እንዲችሉ ይፈቀድላቸዋል።

በ LSS ህግ መሰረት እርዳታ ለማግኘት ግለሰቡ የወረዳው ቋሚ ነዋሪ መሆን አለበት። እንደዚሁም ግለሰቡ ከነዚህ ከሦስቱ ግሩፖች በአንዱ እሱን የሚመስል ነገር መኖር አለበት።

1. የአእምሮ ዘገምተኛ፣ አውቲዝም ወይም እነዚህን በመሳሰሉት የሚጠቁ ሰዎች
2. አዋቂ ሆነው ጭንቅላታቸው ውስጥ በተፈጠረ ጉዳት ምክንያት አካል ጉዳት የገጠማቸው
3. ሌሎች በትልቅ አካል ጉዳት ከመጠቃታቸው የተነሳ ኑሮን በገዛ እራሳቸው መቋቋም የማይችሉ።

የወረዳው መስተዳደር ያ ሰው የሚያስፈልገውን እርዳታ ማዘጋጀት አለበት። ግለሰቡ ራሱ አብሮ በመሆን የሚስማማውን እርዳታ ይወስናል። ልጆችም ጭምር ስለሚያገኙት ድጋፍ ምን እንደሚያስቡ የመናገር መብት አላቸው።

## የጉዞ አገልግሎት

በጋራ ባቡሮችና አውቶቡሶች መሄድ የሚከብደው ሰው ልዩ ድጋፍ የማግኘት መብት አለው። በጉዞ አገልግሎት መጠቀም ይፈቀድላቸዋል። እንደዚሁም ለራሳቸው ተስማሚ የሆነ መኪና እንዲያሰሩ ገንዘብ ይሰጣቸዋል። አንድ ግለሰብ የጉዞ አገልግሎት መብት እንዲኖረው በአብዛኛው የመኖሪያ ፈቃድ እንዲኖረው ያስፈልጋል። ግለሰቡ ዜግነት እንዲኖረው አይጠበቅበትም። ወረዳው የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸውን ሰዎች መደገፍ ሊመርጥ ይችላል።

## **የትምህርት መብት**

በስዊድን ውስጥ ያሉ ልጆች ትምህርት ቤት የመማር መብት አላቸው። ይሄ ሁሉንም ልጆች ይመለከታል። የመኖሪያ ፈቃድ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ለውጥ የለውም። ወረቀት አልባ ልጆችም ስዊድን ውስጥ ትምህርት ቤት የመሄድ መብት አላቸው።

## መዋለ ህጻናት

ህጻናት ልጆች ከአንድ አመት ጀምሮ መዋለ ህጻናት መሄድ ይችላሉ። ምንም እንኳን ወላጆች ስራ ባይኖራቸውም ህጻናት ቢያንስ በቀን ሦስት ሰዓት መዋለ ህጻናት የመሄድ መብት አላቸው። ለእድገታቸው ልዩ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ልጆች ከመዋለ ህጻናት ያገኙታል።

## SFI

የወረዳ አስተዳደሮች ሁሉ ስዊድንኛ ለስደተኞች (svenska för invandrare) ቋንቋ ማዘጋጀት አለባቸው። በዚያ አማካይነት ግለሰቡ ስዊድንኛ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ይማራል። አስፈላጊው ነገር ለስራውና ለቀኑ የሚበቃውን ቋንቋ መናገር መማር መቻሉ ነው።

## ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Gymnasiet)

ወደ ስዊድን የሚመጡ ወጣቶች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመማር መብት አላቸው። አብዛኛዎቹ ልዩ በሆነ የመግቢያ መርህ ግብር (introduktionsprogram) ተብሎ በሚጠራ ስልጠና ይጀምራሉ። 18 አመት ከመሙላቱ በፊት ወደ ስዊድን የመጣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እስኪያጠናቅቅ መማር ይችላል።

እንደዚሁም ሁለተኛ ደረጃ መማር የሚያስችል፣ ስዊድን ውስጥ መቆየት መብት የሚሰጥ አንድ ልዩ ህግ አለ። ለበለጠ መረጃ ስለ ስደተኞች ጉዳይ (Migrationsverket)፣ ትምህርት ጉዳይ (Skolverket) እና FARR የተባለውን ድርጅት ያንብቡ።

## ዩኒቨርሲቲና ኮሌጅ

ስዊድን ውስጥ የሚኖሩ ሁሉ በዩኒቨርሲቲና በኮሌጅ የመማር መብት አላቸው። ነገር ግን የመኖሪያ ፈቃድ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። እንዲሁም ግለሰቦቹ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ማጠናቀቅ አለባቸው።

## የመኖሪያ ቤት መብትን በሚመለከት

አንድ የመኖሪያ ስፍራ ማግኘት ሰብአዊ መብት ነው። መንግስት ይሄ እንዲተገበር ኃላፊነት አለበት። ይሄ ስደተኞችንም ጭምር ይመለከታል። በአንጻሩ ስዊድን ውስጥ ብዙ ሰዎች ቤት አልባ እየሆኑ ነው።

ፖለቲከኞች ለሁሉ ሰው ቤትና አፓርታማ መስጠት እየተሳካላቸው አይደለም። ስዊድን ውስጥ ወረዳዎች መጠለያ የመስጠት ትልቅ ሃላፊነት አለባቸው። ለምሳሌ ያህል ይሄ በማህበራዊ አገልግሎት ህግ ተቀምጧል። ወረዳዎች በእድሜያቸው ጠና ላሉ ሰዎችና በ LSS ህግ ጥላ ስር ለታቀፉ ልዩ ቤቶች ማሰናዳት ይጠበቅባቸዋል።

አንድ ሌላ ህግ ደግሞ ስደተኞች እንዴት ሌላ ቦታ መኖር እንደሚገባቸው ስለ መፍቀድ ይናገራል። በስዊድን ውስጥ ያሉ ወረዳዎች ሁሉ አብረው በመሆን ነዋሪዎቻቸውን በዛ መደገፍ አለባቸው። ወረዳዎች፣ ስደተኞች የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙ በኋላ ቢያንስ ለሁለት አመታት መጠለያ ማዘጋጀት ይገባቸዋል። ቢቻል ከዚያም በላይ መቆየት ቢፈቀድላቸው ይመረጣል። ቢሆንም ግን ይሄ እንደ ግዴታ የተቀመጠ አይደለም።

## ስለ ትርፍ ጊዜና ባህላዊ መብት

ሰዎች እንቅስቃሴ ሲያደርጉና በትርፍ ጊዜያቸው ደስ የሚላቸውን ነገር ሲሰሩ ደህንነት ይሰማቸዋል። ማህበረሰቡ፣ ህዝቡ እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንዲችል ማመቻቸት አለበት።

ወረዳዎችና አውራጃ መስተዳደሮች ስፖርት መስሪያ ቦታዎች እንዲኖሩ፣ ቲያትር የሚገባበት፣ ሙዚቃ የሚደመጥበትና የመሳሰሉ ነገሮችን ማድረግ እንዲቻል ኃላፊነት አለባቸው።

በአገሪቷ ውስጥ በዛ ባሉ ቦታዎች ለስደተኞችና ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች የሚሆኑ ለየት ያሉ አክቲቪቲዎች አሉ።

ህንጻዎቹ (lokalerna) ተደራሽነት ከሌላቸው ግለሰቡ የመሪ ድጋፍ ሊደረግለት ይችላል።

## ስለ ጤና መብት

የጤና መብት ሰብአዊ መብት ነው። ጥሩ ጤና ጥበቃ እንክብካቤን ይመለከታል። ግን ደግሞ በጣም ጥሩ ምግብን፣ ቤትንና ልብሶችንም ይጨምራል።

ብዙ ለጤንነት መጥፎ የሆኑ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ ያህል ብቸኝነት፣ ከገዛ ቤተሰብ ጋር መገናኘት አለመቻልና የገንዘብ እጦት። ሁሉ ሰው ጤንነት እንዲሰማው መብቱ ነው። ለህብረተሰቡም ጭምር ቢሆን ጥሩ ነው።

## የጤናና የበሽታ እንክብካቤ ህግ (Lagen om hälsa och sjukvård)

ለጤናና ለበሽታ እንክብካቤ አንድ ልዩ ህግ አለ። በህጉ ላይ ማህበረሰቡ የትኛውን የህክምና እንክብካቤ መስጠት እንደሚገባው ተቀምጧል ። እንደዚሁም ህጉ ስለ ህጻናት መቋቋሚያ መብት (habilitering) እና ስለ ረጂ መሳሪያዎች ይናገራል።

ስዊድንኛ ቋንቋ የማይችል ግለሰብ ከዶክተር ወይም ከነርስ ጋር ሲገናኝ የአስተርጓሚ መብት አለው።

## ሌሎች ጤና ጥበቃ ነክ ህጎች

ወረቀት አልባ እና ተደብቀው ያሉ ግለሰቦች የተወሰነ ጤና ጥበቃ ሊያገኙ ይችላሉ። ለድንገተኛ በሽታ ህክምና ማግኘት ይፈቀድላቸዋል። ይሄ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ አይደለም።

አንድ ሰው በቀጥታ ለየትኞቹ በሽታዎች ድጋፍ ማግኘት እንደሚችል ማወቅ ይከብዳል። የተለያዩ ሃኪሞች ደንቦቹን በልዩ ልዩ መንገድ ይጠቀሙባቸዋል።

አንድ ሰው በጠና ከታመመ ወይም ከተጎዳ ወደ ማንኛውም ሆስፒታል መሄድ ይችላል። ግለሰቡ እርዳታ የማግኘት መብት ይኖረዋል። በሆስፒታሉ የሚሰሩ ሰራተኞች ወደ ፖሊሶች መደወል አይችሉም።

እድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ሁልጊዜ ነጻ የጤና እና የጥርስ ህክምና የማግኘት መብት አላቸው። ወረቀት አልባ ልጆች ልክ እንደ ስዊድሽ ልጆች አይነት ተመሳሳይ ጤና ጥበቃ ያገኛሉ።

ስዊድን ውስጥ ጥገኝነት ለሚያመለክቱ ሰዎች ልዩ የጤና ጥበቃና የበሽታ እንክብካቤ ህግ አለ።በዚህ ህግ ውስጥ ካሉ ሀሳቦች አንዱ ወደ ስዊድን የሚመጡ ሰዎች ሁሉ በሀኪም መታየት ይኖርባቸዋል የሚል ነው። ምርመራው ነጻ ነው።

ሀኪሞቹ በመጀመሪያው ምርመራ ማሰብ የሚገባቸው የሚታዩና የማይታዩ አካል ጉዳቶችን ለያይተው ማውጣት አስፈላጊ መሆኑን ነው። እንዲህ አይነቱ ነገር ቀጥታ ከታወቀ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍና እርዳታ በፍጥነት ማግኘት ይችላሉ።

## LMA ህግ

LMA ህግ ስለስደተኞችና ለሌሎችም ስዊድን ውስጥ ከለላ ስለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የሚመለከት ነው። ህጉ የመኖሪያ መብትና መጠነኛ የገንዘብ ድጎማ ይሰጣቸዋል። ለዚህ ነገር ሀላፊው ማን እንደሆነ በደንብ ግልፅ አይደለም።

የስደተኞች ባለስልጣን የወረዳና የአውራጃ መስተዳደሮች እርስ በርስ አይስማሙም። በተለይ ተጨማሪ ልዩ እረዳታ ለሚያስፈልጋቸው ማን መክፈል እንዳለበት ሲታሰብ፤ አንዳንዴ ይህ ሁኔታ ግለሰቦች ምንም ድጋፍ እንዳያገኙ ያደርጋል።

በስዊድን ውስጥ ሌሎች ብዙ ህጎች እንዳሉ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። አንድ ህግ LMA ላይ ከሌለ ሌሎች ህጎች ይተገበራሉ።

## ማን ምንን ይሠራል?

ማንኛው ስለየትኛው ነገር ሃላፊነት እንዳለው ማወቅ አስፈላጊ ነው። አሁን በዚያ ዙሪያ እናውራለን።

## የስደተኞች ባለስልጣን (Migrationsverket)

የስደተኞች ባለስልጣን ማን ስዊድን ውስጥ መኖር መብት እንዳለው ይመረምራል። ባለስልጣኑ ሰዎች መልሳቸውን እየተጠባበቁ ሳሉ በምግብ፣ በመጠለያ እና በመጠነኛ ገንዘብ ይረዳል።

የስደተኞች ባለስልጣን ጥገኝነት ለሚያመለክቱ ሰዎች LMA ካርድ መታወቂያ ይሰጣቸዋል። መታወቂያ ካርዱ ግለሰቡ መልሱን በሚጠባበቅበት ወቅት ስዊድን ውስጥ መቆየት እንዲችል ይፈቅዳል። የኢምግሬሽን ቤቶችና አፓርታማዎች የአካል ጉዳት ላላቸው ሰዎች ተስማሚ መሆን ይገባቸዋል።

እንደዚሁም ከባለስልጣኑ የሚለቀቁ መረጃዎች ለሁሉም ሰው ተደራሽነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።ሚግሬሽን አንድ ጥገኛ አመልካች የሚያስፈልጉትን ረጂ መሳሪያዎች እንዴት ማግኘት እንደሚችል ማሳወቅ አለበት።

## የስራ ስምሪት ባለስልጣን (Arbetsförmedlingen)

የስራ ስምሪት ባለስልጣኑ፣ ህዝቡ ስራ ማግኘት እንዲችል ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል። የስራ ስምሪት ባለስልጣን ስዊድን ውስጥ አዲስ ለሆኑ ሰዎች ልዩ አላፊነት አለበት።

በፍጥነት ስራ እንዲኖራቸው ወይም ትምህርት እንዲጀምሩ ይጠበቅባቸዋል። ለስደተኞችና ለሌሎችም በስዊድን ውስጥ ፈቃድ ላገኙ፣ ለመጀመሪያዎቹ ሁለት አመታት ልዩ የሆነ እቅድ አለ። ይህም የመቋቋሚያ መርሀ ግብር ተብሎ ይጠራል።

## የመድህን ባለስልጣን (Försäkringskassan)

የመድህን ባለስልጣኑ ስራ መስራት ለማይችሉ ግለሰቦች ገንዘብ ይሰጣል። ይህም በሽተኞችን፣ በቤት ያሉ ወላጆችን እና የአካል ጉዳተኞችን ይመለከታል።

አንድ ሰው በመድህን ባለስልጣን እርዳታ እንዲያገኝ በስዊድን ውስጥ የሚኖር ወይም የሚሰራ መሆን አለበት። ግለሰቡ በአብዛኛው የመኖሪያ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል። እንደዚሁም የመድህን ባለስልጣን በስዊድን ውስጥ አዲስ ለሆኑና በመቋቋሚያ መርሀ ግብር ውስጥ ለታቀፉ ሰዎች ገንዘብ ይሰጣል።

## **የወረዳና ክፍለ ሀገር መስተዳደሮች (Kommuner och regioner)**

በስዊድን ውስጥ 290 ወረዳዎች አሉ። በወረዳው ውስጥ ያሉት ነዋሪዎች የትኛዎቹ ፖለቲከኞች እንደሚያስተዳደሯቸው ይመርጣሉ።ፖለቲከኞቹ በወረዳው ውስጥ ያሉትን ነዋሪዎች ሁሉ ደህንነት ይጠብቃሉ።

በወረዳው ውስጥ የሚኖሩ ሁሉ ቀረጥ ይከፍላሉ። ገንዘቡ ለትምህርት፣ ለማህበራዊ አገልገሎትና ለመሳሰሉት ይውላል ። በስዊድን ውስጥ 21 ክፍለ ሀገሮች አሉ። ክፍለ ሀገራቱ የጤና ጥበቃ ጉዳዮችን ያስተዳደራሉ። እንደዚሁም የአውቶቡስና የባቡር አገልግሎትም በነርሱ እጅ ነው።

ወረዳዎችና ክፍለ ሀገራቱ ራሳቸውን ችለው ብዙ ነገሮችን ይወስናሉ። ነገር ግን የስዊድን ፓርላማ የሚደነግጋቸውን ህጎች መከተል ይጠበቅባቸዋል።

LSS ህግን ፣ የትምህርት ቤቶች ህግንና የማህበራዊ አገልግሎት ህግን መከተል አለባቸው። የወረዳ አስተዳደሮች ለአካል ጉዳተኛ ስደተኞች ልዩ የሆነ ሀላፊነት አለባቸው።

## የገንዘብ ፍሰት ለወረዳዎች

ወረዳዎቹ በቀረጥ አማካኝነት ገንዘብ ያገኛሉ። እንዲሁም ከመንግስትም ገንዘብ ያገኛሉ። ወረዳዎቹ ለምሳሌ ጥገኞችንና ሌሎች ስደተኞችን በመቀበላቸው የሚያገኙት ገንዘብ አለ።

ፖለቲከኞቹ ልዩ ልዩ ወጪዎችን ማን ይከፈል በሚለው ነገር ስምምነት የላቸውም። ወረዳዎቹ ወይስ መንግስት ነው መከፈል ያለበት?

ይልቁኑ ፖለቲከኞቹ በይበልጥ ስለ ሰብአዊ መብቶችና እንዴት እነዚህን በስራ ላይ ማዋል እንደሚገባቸው መነጋገር በተገባቸው ።

## ማህበራት

በስዊድን ውስጥ ብዙ ማህበራት፣ ድርጅቶችና ሌሎች ግሩፖች አሉ። ለምሳሌ በአካል ጉዳት ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰሩ ብዙ ድርጅቶች አሉ። እንደዚሁም ለአካል ጉዳተኛ ስደተኞችና ለመብቶቻቸው የሚሟገቱ ሌሎች ድርጅቶች አሉ።

ፖለቲከኞችና ባለስልጣኖች ማህበራትንና ድርጅቶችን ማዳመጣቸው አስፈላጊ ነው። እያንዳንዳቸው በጥምረት መስራት ሲችሉ እጅግ መልካም ይሆናል። ብዙዎቹ DRW የሚገናኛቸው ስደተኞች ያለማህበሩ ድጋፍና ያለድርጅቶቹ አንዘልቀውም ነበር ብለው ይናገራሉ።

ቀይ መስቀል አንዱ ምሳሌ ነው። ለብዙ የስነ ልቡና ታማሚ ስደተኞች የጤና ድጋፍ ሰጥቷል። የስዊድን ቤተ ክርስቲያንም ብዙዎች የማህበረሰብ ድጋፍ እንዲያገኙ ማመልከት እንዲችሉ ረድቷል።ለምሳሌ ለአስፈላጊ መድሃኒት ወጪዎች ገንዘብ እንዲያገኙ።

የሚሰጡት እርዳታ እንዲሁ ለብቸኛ መጥ ልጆች ጭምር ርድቷል፤ ለምሳሌ መጠለያ ቤት እንዲያገኙ። FARR የተባለው ድርጅት ለብዙዎች፣ የጥገኞችና ስደተኞች ህጎቹ እንዲገባቸው ርድቷል።

የቋንቋ ካፌዎች ለብዙዎቹ ገና ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የስዊድንኛ ቋንቋ እንዲማሩ እድል ሰጥቶአቸዋል። በተለይ ከአካል ጉዳተኛ ስደተኞች ጋር የሚሰሩ ብዙ ድርጅቶች አሉ።

Hjärnkoll ፣ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር (Hörselskadades Riksförbund)፣ እና ILI ጥቂቶቹ ናቸው ።

DRW እንደሚለው ብዙዎች የሚገናኛቸው ፣ እጅግ በጣም ከፍተኛ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ናቸው። ወደ ስብሰባዎችና የቋንቋ ስልጠናዎች ራሳቸውን ችለው መምጣት በጣም ይከብዳቸዋል። ትርፋማ ያልሆኑ ማህበራት ለአካል ጉዳተኞች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው።

## ህግ አዋቂዎች

በስዊድን ውስጥ እያንዳንዱ ግለሰብ፣ በራሱ ሃላፊነት የሚያስፈልገውን ልዩ ልዩ ጉዳዮች በማመልከት ከወረዳና ከባለሰልጣኖች ጋር ማስፈጸም አለበት ። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ህጎችንና ደንቦችን መረዳት ይከብዳል። ታዲያ ያኔ ግለሰቡ የጠበቃ ድጋፍ ያስፈልገዋል።

አንድ ሰው ስዊድን ውስጥ ለጥገኝነት ሲያመለክት ብዙ ጊዜ ጠበቃ ወይም የህግ አዋቂ ይሰጠዋል።ግለሰቡ ለዚያ መክፈል አያስፈልገውም። ነገር ግን የግለሰቡ ቤተሰቦች ወደ ስዊድን መምጣት ከፈለጉ ጉዳዩ ከዚያ የተለየ ይሆናል። በዚህ ሁኔታ ግለሰቦቹ የህግ አዋቂ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ እራሳቸው መክፈል ይኖርባቸዋል።

አንድ ግለሰብ ከማህበራዊ አገልግሎት አንድ ነገር ሲያመለክት ግለሰቡ ምንም አይነት እርዳታ አያገኝም ። ይህንን ሰውዬው ራሱ መወጣት አለበት ። ነገር ግን አንዳንዴ ወረዳው ውስጥ አንድ ምክርና ጥቆማ የሚሰጥ ሰው ሊገኝ ይችላል።

ብዙ ሰዎች ከባለስልጣናት ጋር ባላቸው ግንኙነት የህግ አዋቂዎች እገዛ ያስፈልጋቸዋል። ብዙ ጊዜ ይሄ በጣም ውድ ነው። አንዳንዴ ማህበራትና ድርጅቶች የህግ ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ። ነገር ግን በአብዛኛው ሁሉን ሰው መርዳት አይችሉም። አንዳንድ በህጎችና በስደት ዙሪያ ድጋፍ የሚሰጡ ድርጅቶች፡

- አምነስቲ ኢንተርናሽናል
- የስዊድን ቀይ መስቀል
- የጥገኝነት መብት ቢሮ
- ስታድስሚሲዮነን
- ካሪታስ
- ነፍስ ወከፍ ሰብአዊ እርዳታ
- የስደተኞች ብሄራዊ መማክርት FARR

አካል ጉዳትን በሚመለከት ህጎች ዙሪያ የሚረዱ አንዳንድ ድርጅቶች፡

- ቡሰ - የምክር፣ ድጋፍና እውቀት ማእከል(Bosse–råd, stöd & kunskapscenter)
- ላሰ የተጠቃሚዎች ድጋፍ ማእከል (LaSSe Brukarstödcenter)



# 3. ችግሮችና ሊሻሻሉ የሚገባቸው

DRW ከብዙ አካል ጉዳተኛ ስደተኞች ጋር አውርቷል። ትረካዎቻቸው የሚያሳየው ስለችግሮቻቸውና ሌሎችም በጥሩ ሁኔታ ስለሚከናወኑ ነገሮች ነው። በዚህኛው የመጽሐፍ ክፍል በችግሮችና ለመፍትሄ በሚሆኑ ሀሳቦች ዙሪያ የምናወራ ይሆናል።

## ብዙዎች ጤንነት አይሰማቸውም

መሰደድ ትልቅ ለውጥ አምጪና በጣም ለውጥረት የሚዳርግ ነው። እንዲያውም ውጥረቱ ወደ አእምሮ መታወክ (psykos) ሊያመራ ይችላል ። ከሌሎች ሰዎች ጋር መገናኘትና ከራስ ቤተሰብ አጠገብ መሆን አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ለብዙ በስዊድን ውስጥ ላሉ ስደተኞች የማይቻል ነው ።

አካል ጉዳተኛ ስደተኞች ብዙ ጊዜ ከሌሎች የበለጠ ብቸኝነት ይሰማቸዋል። ከሌሎች ጋር የሚገናኙበት ቦታ ለማግኘት ይከብዳቸዋል ። የስዊድንኛው ስልጠና ለነሱ የሚስማማቸው አይደለም ። የተሽከርካሪ ወንበር (rullstol) ተጠቃሚዎች ምናልባት እስከ አነካቴው ከቤት መውጣት ላይችሉ ይችላሉ።

ስዊድን ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ የሚሰጡ ብዙ ጥሩ ህጎች አሏት።ነገር ግን ህጎቹ የመኖሪያ ፈቃድ የሌለውን አይመለከትም ።

ችግሮቹ ብዙ ጊዜ ለመጀመሪያዎቹ አመታት ይቀጥላሉ። ለአዲስ መጤዎች የሚሰጠው ድጋፍ ለሁሉ አይደለም የሚስማማው። የዚያም ውጤት ስዊድን ውስጥ ያሉ የአካል ጉዳተኞች ስደተኞች ከባድ ኑሮ እንዲመሩ ይገደዳሉ።

የተሻለ ፖለቲካና ህጎች ይህንን ሁኔታ ሊለውጡ ይችላሉ።

## ታሪኮች

DRW ስዊድን ከመጡበት ጊዜ አንስቶ ጀምሮ ከእንቅፋት ተላቀው ከማያውቁ ስደተኞች ጋር ይገናኛል። በቅድሚያ ስለመኖሪያ ፈቃድ እርግጠኞች አይደሉም። በዚያም ላይ እርዳታና ድጋፍ ለማግኘት የሚደረገው ትግል ይጀምራል። ብዙዎቹ ሁኔታው ተስፋ እንደሌለው ይሰማቸዋል።

የመኖሪያ ቤት ሳይስማማ ሲቀር ሰውነት ይጎዳል። የዕለት ከዕለት ኑሮን መምራት እራሱን የቻለ ትግል ሊሆን ይችላል። ወደ ስዊድንኛ ትምህርት መምጣቱ የሚከብድ ይሆናል ። የምግብ ጥሬ እቃዎችን ገዝቶ ከረጢቶቹን ተሸክሞ ቤት ማድረስ ይከብዳል። ብዙዎቹ የመኖሪያ ፈቃድ እንደማያገኙ እና ቤታቸውን እንዳያጡ ይፈራሉ። መተኛት ይከብዳቸዋል፣ ጥሩ ጤንነትም የላቸውም።

ይሄ ሁሉ ወደ ውጥረትና ወደከፋ የጤና ቀውስ ይመራቸዋል። በዚህ ሁኔታ ህይወታቸውን በስዊድን ውስጥ መጀመርና የማህበረሰቡ አካል መሆን ይከብዳቸዋል።

በመቀጠል ሰዎች በስዊድን ውስጥ ስለገጠማቸው ሁኔታዎች ጥቂት ትረካዎች እንመልከት። ትረካዎቹ DRW ከተገናኛቸው ግለሰቦች የመጡ ናቸው።

**የግል እንክብካቤ አይፈቀድለትም።**

አንድ ሰው የከፋ የጀርባ ጉዳት አለበት። የማያቋርጥ ውጋትና ከባድ የመንቀሳቀስ ችግር አለበት።

ሰውየው ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ አለው፣ ሆኖም ግን ትክክለኛ እርዳታ የለውም። የሚረዳው የግል እርዳታና ከቤቱ ለመውጣት የመጓጓዣ አገልግሎት ያስፈልገዋል። ባለስልጣኖቹ ድጋፍ የማግኘት መብት የለውም ይላሉ። ያለ ድጋፍ ሰውዬው ለልጆቹ ጥሩ ወላጅ መሆን አይችልም ። እንደዚሁም ለዚህ ሰው የአዲሱ ማህበረሰብ አካል መሆን ይከብደዋል።

**ከልጆቿ ጋር መገናኘት አይፈቀድላትም።**

አንዲት ሴት ወደ ስዊድን በጥገኝነት መጥታለች። ሁለት ልጆቿም ወደ ስዊድን እንዲመጡላት ትፈልጋለች። ሰባትና ዘጠኝ አመት ናቸው።

የስደተኞች ባለስልጣን አይሆንም ይላታል። ሴትየዋ ስራ የላትም፣ በቂ ስፋት ያለው መኖሪያ ቤትም የላትም። ሴትዬዋ አካል ጉዳተኛ ነች። ለመማርና ለመስራት የሚያስፈልጋትን ድጋፍ አላገኘችም።

ወደ ስዊድን አዲስ ለመጡ ሰዎችና ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች አገሪቱ ውስጥ ስራ ማግኘት ከባድ ነው። ሴትዬዋ በሁለቱም ውስጥ አለችበት። ስዊድን ውስጥ አዲስ ለሆኑ ሰዎች የሚሰጡ ስራዎች ብዙ ጊዜ ለሰውነት የሚከብዱ ናቸው። ሴትዬዋ እንደዚህ አይነቱን ሥራ መስራት አትችልም።

ቤተሰቡ ለአምስት አመታት አንድ ላይ አልኖሩም። እንደገና መቼ እንደሚገናኙም አያውቁም። ሁሉም መጥፎ ነገር ይሰማቸዋል።

ሰው ሁሉ ከቤተሰቡ ጋር ይሆን ዘንድ ሰብአዊ መብቱ  ነው። ስዊድን ያንን መብት ለሴትዬዋና ለልጆቿ እየሰጠች አይደለም። ከልጆቿ ጋር የመሆኗ እድል ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲወዳደር በጣም የከፋ ነው።

በሁኔታዋ፣ የአድሎአዊ ደንቦች ሰለባ ስለሆነች ምንም ለማድረግ አልቻለችም። እንደዚሁም አካል ጉዳተኛ ስደተኞች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉበት ሁኔታ እናሳ መሆኑን ያሳያል።

**ስዊድንኛ መማር አይችልም።**

አንድ አይነ ስውር የሆነ ሰው ስዊድንኛ ለመማር ይፈልጋል። ይሁንና ለመማር የሚያስፈልገውን ተጨማሪ እርዳታ አያገኝም። ስለዚህ ሰውዬው በስዊድን ውስጥ፣ ለመነጋገር እንዲችል ሌሎች ሰዎች ያስፈልጉታል። ብዙ ጊዜ ማንም የሚረዳው የለም።

ሰውዬው ብዙ ጊዜ ቤቱ ስለሚሆን ብቸኝነት ያጠቃዋል። በቁዘማ ይመታል ፣ ጥሩ እንቅልፍ የለውም፣ እራሱን እንደ መጥፎ ሰው አርጎ ያያል። የስዊድንኛ ቋንቋ ለስደተኞች (SFI)፣ ለአካል ጉዳተኛ ስደተኞች የሚስማማ አይደለም።

ለነሱ ተስማሚ የሆኑ መጽሐፎች የሉም። ወደ ትምህርት ቤት ለመምጣት ሆነ በትምህርታቸው ተጨማሪ እርዳታ አያገኙም። ባለስልጣኖቹ ስለ አካል ጉዳትና በአካል ጉዳት ጥያቄዎች ዙሪያ ስለሚመጡ እንቅፋቶች ብዙ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል።

**ቤታቸውን ለቀው ለመሄድ ተገደዱ**

አንዲት ሁለት ልጆች ያላት ሴት በስዊድን የሚኖራት የመጀመሪያዎቹ ሁለት አመታት በስቶክሆልም እንደሚሆን ተረዳች። ሴትዮዋ የፖሊዮ ጉዳተኛ ነች። ከመቅጽፈት፣ቤተሰቦቿ ሁለት አመት ባይሞላቸውም ወደ ቬስተርኖርላንድ ሊቀይሩ ግድ ሆነ።አዲሱ መኖሪያ ቤት ለሴትዮዋ አልተስማማትም። ተደራሽነት ያለው አልነበረም።ለሱቆች፣ ለትምህርት ቤቶች፣ ለህክምናና ለሌሎችም አገልግሎቶች የራቀ ነበር ።

ሴትዮዋና ልጆቹ ብቻቸውን ቀሩ። በስዊድንኛ ስልጠናዎቹ ሊሳተፉ አልቻሉም። ሴትዮዋ ጉዳትዋ ተባብሶ የበለጠ ችግር ገጠማት።

በስዊድን አዲስ የሆኑ፣ ብዙ ጊዜ የመኖሪያ አካባቢ መቀየር እንደሚገባቸው የተለመደ ነው። ራቅ ወዳለ አውቶቡስ ወይም መኪና ወደማይገኝበት ገጠራማ ቦታ ሊመደቡ ይችላሉ። ይህ ሁኔታ ከአዳዲስ ሰዎች ጋር መተዋወቅን እጅግ ከባድ ነገር ያደርገዋል። ሥራ ማግኘት እና ስዊድንኛ መማር ከዚያ የበለጠ ከባድ ይሆናል።

**የጋራ አካታች ስርዓት እንቅፋቶች (Hinder för ömsesidig integration)**

ስለ ስዊድን ያለው ስዕል ለሁሉም ክፍት የሆነች፣ እኩልነትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት የሚል ነው። ነገር ግን እንደሚገባ ያልሆኑ ነገሮችም እንዳሉ በድፍረት መናገር አለብን። እነዚህን ነገሮች ለማየት ድፍረት ካለን ማህበረሰቡን የተሻለ ማድረግ እንችላለን።

ስዊድን ውስጥ አዲስ የሆኑ ሰዎች በአብዛኛው ረዘም ላለ ጊዜ ከኖሩት ይልቅ በከፋ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ። ከበድ ያሉ ሁኔታዎች ይጠብቃቸዋል። በተለይ አንድ ሰው ከቤተሰቡ ጋር መኖር የሚፈልግ ከሆነ ።

አካል ጉዳት  ያለባቸው ስደተኞች የበለጠ ከባድ ጫና አለባቸው። ለስደተኞቹ የሚሰጠው ድጋፍ ለነሱ የሚስማማ አይደለም።

ይሄ ብዙ ጊዜ የማህበረሰቡ እኩል ተሳታፊ አካል ከመሆን ይልቅ፣ ወደ ብቸኝነትና መገለል ያመራል። ከዚህ በታች ግሩፑ ከሚገጥማቸው ችግሮች ጥቂቶቹን እንነግራችኋለን።

**<u>ፊት መነሳት  (Dåligt bemötande)</u>**

ብዙዎች እንደነገሩን፣ የስደተኞች ባለስልጣን ሰራተኞች በመጥፎ መስተንግዶ እንደሚቀበሏቸው ነው።

ለምሳሌ ብዙዎቹ እንደሚሉት፣ ሰራተኞችን እርዳታ ሲጠይቋቸው ነገሩ የምር እንደሆነ አያምኗቸውም። *" እስከ ስዊድን ደረስ ረጂሙን መንገድ ከመጣህ ፣ እስከ ሆስፒታሉም ደረስ መሄድ ትችላለህ!"*

**<u>የመረጃ እጥረት</u>**

አካል ጉዳተኛ ስደተኞች ስለመብቶቻቸው መረጃ አያገኙም። የመረጃ ተደራሽነት የለም።

ነገሩ የመኖሪያ ፈቃድም ካገኙ በኋላ ይቀጥላል። ከሌሎች እኩል የሆነ ጤና ጥበቃ እንክብካቤ አያገኙም። መረጃውን ለመረዳት ከባድ ነው እንዴት የድጋፍና የአገልግሎት ማመልከቻ ማስገባት እንደሚችሉ አያውቁም።

**<u>የተዘጉ ቦታዎች</u>**

ብዙ ቦታዎች ለአካል ጉዳተኛ ስደተኞች ዝግ ናቸው። በከፊል በቋንቋው ምክንያት። በከፊል በቦታዎቹ ተደራሽነት እጦት ምክንያት።

**<u>መልስ መጠበቅ</u>**

በስዊድን ውስጥ ከለላ የሚፈልጉ ሁሉ ፍትህዊ የሆነ ጥናታዊ ምርመራ ያስፈልጋቸዋል። ይህንን እንዳላገኙ የሚሰማቸው ብዙ ጊዜ እጅግ በከፋ ጤንነት ላይ ይገኛሉ። መልሳቸውን እየተጠባበቁ እያለ አንድ የሆነ የሚሰሩት ነገር ቢኖር መልካም ይሆናል። እንደዚሁም በህጎችና ደንቦች ዙሪያ በስዊድን ውስጥ ምን አይነት እርዳታ ሊያገኙ እንደሚችሉ ጥሩ መረጃ ያስፈልጋቸዋል።

ይሄ ጊዜ የሚመቻቸው ከሆነ፣ ሰዎች የመኖሪያ ፈቃድ ሲያገኙ የስዊድን ህይወታቸው አጀማመር ምናልባት ይቀልላቸዋል።

**መጥፎ ስርአቶች**

የስደተኞች አቀባበል ስርአትን የዘረጉት ሰዎች የአካል ጉዳት ጥያቄዎችን ወይም አመለካከትን አላሰቡበትም። ይህም ለምሳሌ የስዊድንኛ ቋንቋ ትምህርቶችንና የስራ ስምሪት መቋቋሚያ መርህ ግብርን ይመለከታል። ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች የተቀረጹ አይደሉም።

**ከአመጻ መታደግ (Skydd mot våld)**

እንደዚሁም የአካል ጉዳት ተጠቂ ሰዎች ሌላ ልዩ ከለላ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ለአመጻና አድልዎ የመጋለጣቸው አደጋ ከፍ ያለ ነው።

በተለይም ሴቶች አረጋውያንና ልጆች እንደዚሁም አካል ጉዳተኛ ግብረ ሰዶማዊና መሰል ጾታዊ ልምምድ አራማጆች ( HBTQ) ከፍ ላለ አደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ። እነዚህ ግሩፖች አስፈላጊው ከለላና ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል።

**አካታች ስርዓትና መስፈርቶቻቸው (Integration och krav)**

አካታችነት፣ የማህበረሰቡ አካል መሆንን ይመለከታል ። ስራ፣ መጠለያና በአዲሱ አገር ጓደኛ ማግኘትን ያካትታል። ተቃራኒው አድሎነት ነው። በአሁኑ ጊዜ ስዊድን ውስጥ ብዙ አድልዎ አለ።

ለዚህም አንዱ ምክንያት የቤቶችና የመኖሪያ ደንቦች ናቸው። የመኖሪያ ቤቶቹ ለመግዛትም ይሁን ለመከራየት በጣም ውድ ናቸው።

በስዊድን ውስጥ በዛ ያሉ ልጆች ድሆች ናቸው። በተለይ ወላጆቻቸው ከሌላ አገር የሆኑ ልጆችን ይመለከታል። ፖለቲከኞች በአደንዛዥ ዕጽና በወንጀል ችግር ስለተጨናነቁ፣ ከከተማ ወጣ ብለው ስላሉ ድሃ ክፍለ ከተሞች ብዙ ያወራሉ። ብዙ ጊዜ ችግሮቹን በስደት ላይ ያመካኛሉ።

ሁሉን ችግር በአንድ በተወሰነ ሰዎች ግሩፕ ላይ ማመካኘት ዘረኝነት ነው። አንድን ግሩፕ ከሌላ ግሩፕ ጋር ማፋጠጥ ይሆናል። ይሄ አደገኛ ነው ! በፖለቲካው ዓለም ብዙ ጊዜ፣ "ስደተኞች ራሳቸውን ፍትህና ዲሞክራሲ ከሰፈነባት ስዊድን ጋር ያለማምዱ" ሲባል እንሰማለን። መስፈርቶችን ማስቀመጡ ጥሩ ሊሆን ይችላል። ሰዎች በፍጥነት ቋንቋውን ተምረው የማህበረሰቡ አካል እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል። ነገር ግን መስፈርቶቹ መተግበር የሚችሉ መሆን አለባቸው። ሰዎች የሚኖሩበትን ተጨባጭ ሁኔታዎች ያገናዘቡ መሆን ይገባቸዋል።

**ባስፈላጊነት ሊታሰብባቸው የሚገቡ**

ባለስልጣኖች በተራ ሰዎች ላይ ስልጣን አላቸው። በተለይ ድጋፍ በሚያስፈልጋቸው ሰዎች ላይ ። ይሄ ሊታሰብበት ያስፈልጋል። ባለስልጣኖች ከአካል ጉዳተኞች ጋር በምን አይነት መንገድ እንደሚገናኙ ማሰብ አለባቸው።

**ባህላዊ ልዩነቶች**

በተለያዩ ባህል ውስጥ ያሉ ሰዎች አካል ጉዳትን በልዩ ልዩ መንገድ ያያሉ። በስዊድን ውስጥ አካል ጉዳተኛ ሰዎች እርዳታና ድጋፍ ማግኘት እንደሚገባቸው በህጉ ላይ ተቀምጧል። እንደዚሁም ሰዎች ሁሉ በማህበረሰቡ ተሳታፊ እንዳይሆኑ የሚያደርጉ እንቅፋት የሆኑ ህጎችን ለማስወገድ እንሞክራለን።

ዳሩ ግን እንዳጋጣሚ ብዙዎች አሁንም ድረስ፣ አካል ጉዳትን እንደ አንድ መጥፎ ነገር ያዩታል ። ከበሽታና ከተፈጥሮ ጉዳት ጋር ያገናኙታል። ሁሉ ሰው ስለራሱ ባህል ማሰቡ አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ስለ ባህላችን ማጤን እንድንችል ይፈቅድልናል።

**ሃፍረት በሁሉም ባህሎች ውስጥ አለ።**

ልዩ ልዩ ቋንቋዎችና አሰራሮች በእኩልነት መታየት እንዲችሉ በስዊድን ውስጥ ትላልቅ ለውጦች ያስፈልጋሉ።

**ኖርሞቹን መቀየር ያስፈልገናል**

ለዚህም አይነተኛው መንገድ፣ እራሳቸው ወደ ስዊድን ከመጡት አካል ጉዳተኛ ስደተኞች ጋር በመተባበር ነው። እነሱ አዋቂዎች ናቸው።

**ነገር እንዳሰቡት ሲሆን**

ከዚህ ቀጥሎ ከሁለት አመት በፊት ወደ ስዊድን የመጣ ስደተኛ ሰው ይሄን አጫወተን። *" ከብዙ አመታት በፊት አንድ እግሬን አጣሁኝ፡ ከዚያም በሁለት ክራንቾች መሄድ ጀመርኩ። ሁኔታው ለሁለተኛው እግሬ እጅግ አሰልቺ ነበር "።*

እዚህ ስዊድን ውስጥ ራሴን በመቻልና የራሴን ሕይወት ለመምራት በመወሰን ብዙ እርምጃዎችን አይቻለሁ።

ለዚህም ዋና ምክንያቱ በተሻለ መሄድ እንድችል የሚያደርግ አንድ ፕሮቴስ ስለተሰራልኝ ነው። አሁን ፣የምጠቀመው አንድ ክራንች ብቻ ስለሆነ አንድ ነጻ እጅ አለኝ።

አሁን በቀላሉ መማር፣ የስራ ልምምድ ማድረግና መስራት እችላለሁ። በቅርቡ ትክክለኛ ስራ እንደማገኝ ተስፋ አለኝ ። የጤና ጥበቃ ዘርፍና የሸሌፍቲዮ መስተዳድር በመተባበር ይሄ ነገር እውን እንዲሆን ስላደረጉ ደስተኛ ነኝ።

እንደዚሁም DRW ከተለያዩ ወረዳ መስተዳደሮችና ባለስልጣኖች ጋር በመወያየት ለብዙ ችግሮች መፍትሄ ማግኘት ችሏል። የላቀ እውቀትና አዲስ እይታ መስጠት እንደምንችል ተስፋ እናደርጋለን።

*"ለጉዞ አገልግሎት ማመልከቻዬ አይሆንም የሚል መልስ አገኘሁ"።*

ከ DRW የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች ጋር ሆነን አንድ ማመልከቻ አስገባን። ጉዳዩ፣ የስራው ጸባይ የመጓጓዣ አስፈላጊት ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር። ወዲያውኑ የጉዞ አገልግሎት (färdtjänst) ተፈቀደልኝ።

## **የጥምረት ስራ ሃሳቦች**

በዚህ መጽሐፍ ብዙ ጊዜ ደጋግመን በባለስልጣኖችና በሌሎችም መካከል የበለጠ የጥምረት ስራ እንደሚያስፈልግ ጽፈናል ። በአካል ጉዳትና በስደት ዙሪያ የሚሰሩ ልዩ ልዩ እውቀትና የስራ ልምድ ያላቸውን ድርጅቶች ማዳመጥ አስፈላጊ ነው።

ስለዚህ ከጥገኝነት መብት እንቅስቃሴ ጋርና ከአካል ጉዳት መብት ድርጅቶች ጋር ተባብሮ መስራት አስፈላጊ ነው። ሁሉንም ስርአትንና አስተሳሰብ በጥራት መቆጣጠር መቻል ከባድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በጥሩ ጥምረት ስራ እውቀቱ ለብዙዎች ሊሰራጭ ይችላል።

አንዱ ሃሳብ በበይነ መረብ አንድ መድረክ መፍጠር ይሆናል። በዚያም መድረክ፣ ማቴሪያሎችን መሰብሰብና እርስ በርስ መነጋገር ይቻላል። መድረኩ፣ ባለስልጣኖች ከአካል ጉዳትና ከፖለቲካ ጥያቄዎች ጋር የሚሰሩ ሰዎች የሚገናኙበት ሊሆን ይችላል።

እንደዚሁም አብሮ መስራት በስዊድን ወስጥ አዲስ ለሆነ ሰው እቅድ ለማውጣት ጥሩ ነው።

## የኛ ሃሳቦች

ከዚህ በመቀጠል DRW ይህን መጽሐፍ ሲያዘጋጅ የደረሰባቸውን ሃሳቦች ዝርዝር ያስቀምጣል።

እነዚህ ሃሳቦች፣ ወደ ስዊድን ለሚሰደዱና አካል ጉዳት ላላቸው ሰዎች የተሻሉ እድሎች ሊሰጡ እንደሚችሉ እናስባለን።

ሃሳቦቹ

- በቤተሰቦች መዋሃድ ዙሪያ ያሉት ህጎች ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ ሆነው መለየት ያስፈልጋቸዋል። ማህበረሰቡ ለአካል ጉዳተኞች የተመቸ አይደለም። ስለዚህ ስራና መኖሪያ ቤት ማግኘት የበለጠ ይከብዳቸዋል። እነዚህን ነገሮች ህጎቹ ትኩረት ውስጥ ማስገባት አለባቸው ።
- አካል ጉዳት ያላቸው ሰዎች በስዊድን አዲስ ኑሮ መጀመር እንዲችሉ ከሁለት አመት የበለጠ ጊዜ ስጧቸው። ረዘም ላለ ጊዜ ትምህርት፣ መኖሪያ ቤትና ስራ የማግኘት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።
- የትዳር አጋር ሆነው ወደ ስዊድን የሚመጡ የአካል ጉዳተኛ ስደተኞች ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። በመቋቋሚያ መርሀ ግብር ውስጥ መካተት ሊፈቀድላቸው ይገባል።
- ለጥገኝነት የሚያመለክቱ አካል ጉዳተኞች ለነሱ ምቹ በሆነ መንገድ የቤቶች መብትና የጉዞ መብት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።
- ለስደተኞች የሚሰጠው የጤና ምርምራ የአካል ጉዳት እይታ እንዲኖረው ያስፈልጋል። በዚህ መንገድ ከወዲሁ ማን ምን አይነት ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ግልፅ መሆን ይችላል።
- ሰዎች ራሳቸው የሚፈልጉትን ይናገሩ ። ፍላጎቶቹ በህይወት ሂደት ውስጥ ሊቀየሩ ይችላሉ።
- ልጆችም የሚያስቡትን ነገር የመናገር መብት ሊኖራቸው ይገባል። ልጆች ለነሱ ሊገባ የሚችል መረጃ ማግኘት አለባቸው። ለልጅ የሚበጀው ማእከላዊ ትኩረት መያዝ አለበት።
- የስዊድንኛ ቋንቋ ስልጠና (SFI) ለሁሉ ሰው መስራት አለበት። መገናኛ ቦታዎች ፣ መጻህፍትና ሌሎችም ማቴሪያሎች ተደራሽ መሆን አለባቸው።
- ለስዊድን ባለስልጣናት ሰራተኞች ትምህርት ይሰጣቸው። ማንም ሰው ያለ አግባብ ኢፍታሃዊነት እንዳይደርስበት ። ማንም ሰው ጸያፍ ቃላት ወይም አገላለጽ አይጠቀም።
- ባለጉዳይ በሚቀለው መንገድ ሃሳቡን መግለጽ እንዲችል ይፈቀድለት። ምናልባት ግለሰቡ፣ አስተርጓሚ፣ የምልክት ቋንቋ፣ የምልክት ድጋፍ፣ የብሬል ወይም ሌላ አይነት ድጋፍ ሊያስፈልገው ይችላል።
- የስደት ባለስልጣን አካል ጉዳተኞችን ለመቀበል ከፈቀደ የወረዳ መስተዳደር ጋር ጥሩ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። ወረዳው ተስማሚ መኖሪያ ቤት፣ ድጋፍና ሌላም አገልግሎት ማቅረብ እንዲችል መረጃ ማግኘት አለበት።

- መጠለያ ቤቱ ለብቻው ገለል ያለ መሆን የለበትም። ከሌሎች ሰዎች ጋር መገናኘት እንዲቻልና ለስዊድንኛ ትምህርትም የሚያመች መሆን አለበት።
- ስደተኛ አካል ጉዳተኞች የስዊድን ማህበረሰብ ስርአት እንዴት እንደሆነና በቀጣይነት የነሱ የኑሮ ሂደት ምን እንደሚሆን ቶሎ ብለው መረጃ ማግኘት ይገባቸዋል ።
- ባለስልጣኖች ሰዎች በሚገባቸው መንገድ ስለመብቶች ማስረዳት አለባቸው። የጽሑፍ ትርጉሞችና የተለያዩ አይነት አስተርጓሚዎች መኖር አለባቸው።
- አካል ጉዳተኛ ስደተኞች የሚያስፈልጋቸውን ማግኘት እንዲችሉ በቂ ገንዘብ እንዳለ ማየት ይገባል።

<u>አስፈላጊ መጽሐፍ</u>

UNHCR የተባበሩት መንግስታት አንዱ አካል ድርጅት ነው። አካል ጉዳተኛ ስደተኞችን ለሚቀበሉ አገሮች ጥቆማ የሚሰጥ አንድ መጽሃፍ ጽፏል።

እነርሱ እንደሚጽፉት ይህን ግሩፕ ማንም እንደማያስበው ትልቅ አደጋ አለ። ብዙ ጊዜ ያለ ምንም ድጋፍና አገልግሎት ይቀራሉ። አካል ጉዳተኛ ስደተኞች ሌሎች ስደተኞች የሚያገኙትን ሁኔታዎች በእኩልነት ማግኘት ይገባቸዋል። አድሎ ሊደርስባቸው አይገባም።

መጽሐፉ፣ አገራቱ የትኞቹ ስደተኞች እንዴት ተጨማሪ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው የሚያውቁበትን መንገድና ግሩፑን እንዴት በተደራሽነት መንገድ መቀበል እንደሚቻል ጥቆማ ይሰጣል።

መጽሐፉ ከዚህ ስር ባለው ድረ ገጽ ይገኛል።

http://swigea56.hcrnet.ch/refworld/ docid/5163f43e4.html

# 4. መደምደሚያ

አካል ጉዳተኛ ስደተኞች ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ አመለካከታችን ቅይጣዊ (intersektionellt) መሆን አስፈላጊ ነው። ይህም፣ እንዴት ስደትና አካል ጉዳት በተመሳሳይነት እርስ በርስ እንደሚጣመሩ ማየትን ይመለከታል።

እንደሌሎቹ ጥሩ ህይወት፣ እኩል መብቶችና እድሎች አላቸው። ለአድሎት መጋለጥ አይገባቸውም።

ስዊድን ከሌሎቹ አገሮች ጋር ሲወዳደር ወደፊት ተራምዳለች። ነገር ግን ብዙ የሚሰራ ሥራ ይቀራል ።ማህበረሰቡ በዚህ ግሩፕ ላይ የበለጠ አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅበታል ።

እነርሱንና ከነርሱ ጋር የሚሰሩትን ድርጅቶች ማዳመጥ ያስፈልጋል።

ባለስልጣኖችና ፖለቲከኞች በስደት ፖለቲካ ውስጥ የበለጠ ስለ አካል ጉዳት ጥያቄዎች ማሰብ ይገባቸዋል። በጣም አንገብጋቢው ነገር ሰብአዊ መብቶች መሆን አለበት።

በገንዘብ ትርፋማ ወይም ቆጣቢ ከመሆን በፊት ይሄ መቅደም ይገባዋል።

ስዊድን ይህንን በብዙ አለማቀፍ ውሎች ቃል ገብታለች። ይሄ ፖለቲካን የሚመለከት ቢሆንም፣ ባለስልጣኖችም በአንድ ግለሰብ ነገር ላይ እንደሚወስኑ ያሳያል።

**ማህበረሰቡ ወደ ስዊድን የተሰደዱ አካል ጉዳተኛ ሰዎችን የበለጠ ማዳመጥ አለበት። ወደ ሁለንተናዊ አካታች ስርአት ለመድረስ ያለው ብቸኛ መንገድ ይሄው ነው ።**

የስዊድንኛውን ማጣቀሻ ከዚህ በታች እንዳለ ይመልከቱ።

## ማጣቀሻ (Referenslista)


- Riksrevisionens rapport om uppföljning av deltagare i förberedande och orienterande utbildning inom etableringsuppdraget. Skr.2018/19:13
- https://www.regeringen.se/regeringenspolitik/nyanlandas-etablering/
- Health Literacy - teori och praktik i hälsofrämjande arbete: av Karin C. Ringsberg, s. 29.
- https://www.ohchr.org/en/hrbodies/ crpd/pages/crpdindex.aspx
- http://docstore.ohchr.org/SelfServices/ FilesHandler.ashx
- https://spraktidningen.se/blogg/veckansnyord-nyanland
- KOMHIT flyktingmaterialet, har samtalskartor med kompletterande bildstöd för olika situationer, dessa är översatta till 10-11 språk.
- 1 § i lagen samt lagens utformning som inte ger rättigheter
- https://www.regeringen.se/4acfa2/contentassets20b5b-3b157714783a90b f56f5361a74e/181901300webb.pdf s. 4
- https://disabledrefugeeswelcome.se/en/2019/03/english-DRW:sobservations-on-the-situation-ofdisabled-asylum-seekers-in-sweden/
- https://www.regeringen.se/ artiklar/2017/11/fragor-och-svar-ominforandet-av-det-nya-regelverket-foretableringsinatser-for-vissa-nyanlandainvandrare/
- https://www.unhcr.org/protection/ resettlement/51de6e7a9/refugeesdisabilities-unhcr-resettlementassessment-tool.html
- http://dok.slso.sll.se/TC/3_ Vara_kunskapsomraden/ TP/Kulturformuleringen/ Kulturformuleringen_09.pdf
- SOU 2019:23 Styrkraft i funktionshinderspolitiken
- https://www.dagenssamhalle.se/debatt/ segregationen-och-klyftorna-bordeoroa-langt-fler-17594
- Barnfattigdom i Sverige: Årsrapport 2018: https://resourcecentre.savethechildren.net/node/14233/pdf/ rb_rapport_2018_final.pdf
- http://www.antirasistiskaakademin.se/ kulturrasism/

- http://www.mfd.se/globalassets/dokument/publikationer/rapporter/2017/2017-20-funktionsnedsattning-asyletableringsprocessen.pdf
- http://www.manskligarattigheter.se/ Media/Get/526/ladda-ner-dokumentpdf
- Health Literacy - teori och praktik i hälsofrämjande arbete: av Karin C. Ringsberg.
- WHO, 2005: styrdokument för den globala hälsofrämjande konferenser i Bangkok Charter, s.1.
- Hälsans bestämningsfaktorer (Whitehead and Dahlgren,1991)
- Nyanländas hälsa – sammanställning utifrån ett urval av rapporter 2016
- SIOS- Identifiering av funktionsnedsättning/trauma, s. 12
- http://fhie.se/
- http://swigea56.hcrnet.ch/refworld/docid/5163f43e4.html

**የስዊድንኛውን የግርጌ ማስታወሻ ከዚህ በታች እንዳለ ይመልከቱ።**

## የግርጌ ማስታወሻ (Slutnoter)

1. https://www.ohchr.org/en/hrbodies/crpd/pages/crpdindex.aspx

2. Health Literacy - teori och praktik i hälsofrämjande arbete: av Karin C. Ringsberg, s.28.

3. Health Literacy - teori och praktik i hälsofrämjande arbete: av Karin C. Ringsberg.

4. Sammanställning hälsoläget bland nyanlända, s. 7.

5. Riksrevisionens rapport om jämställdhetsintegrering av integrationspolitiken skr. 20181997, s. 5

6.Situationen på arbetsmarknaden för personer med funktionsnedsättning 2017, s. 8

7.https://www.ohchr.org/EN/HRBodies/CRPD/Pages/ConventionRightsPersonsWithDisabilities.aspx

"ሁንተናዊ አካታች ስርዓት ለሁሉ" (Integration för alla)፣ በቀላል ስዊድንኛ DRW የጻፈው የመረጃ መምሪያ ክፍል ሲሆን፣ የዋናው መጽሐፍ ርዕስ "ወደ ጋራ አካታች ስርዓት የሚመሩ መንገዶች" (Vägar mot ömsesidig integration) ይባላል።መጽሐፉ በሙያቸው ከአካል ጉዳተኛ ስደተኞች ጋር ለሚገናኙ ሁሉ አካል ጉዳትን ባካተተ አመለካከት እንዲሰሩ ድጋፍ ይሰጣል።

እንደዚሁም መጽሐፉ፣ አንድ ተደራሽነት ያለው አቀባበል ማቋቋምና አንድ ግሩፑን ያማከለ የጋራ ተሳትፎ እንዴት መስራት እንደሚቻል ምክርና ትጥቅ ይለግሳል።

የመጽሐፉ ዋና ፅንሰ ሃሳብ፣ሰዎች ሁሉ የትኛውም አካል ጉዳት፣ጾታ፣ጾታዊ ማንነት፣ጾታዊ ግንኙነት፣ብሄር፣እድሜ፣የምጣኔ ሀብት ደረጃ፣የስደት ስቴተስ ወይም ሃይማኖት ቢኖራቸው፣ እኩል ክብርና መብቶች አላቸው የሚል ነው።

Independent Living Institute
independentliving.org

MED STÖD FRÅN ALLMÄNNA ARVSFONDEN